ኤፍራታ የድንግል የማርያም ባሪያ
የከበሮ ክፍል ምሳሌያዊ ትርጉም
የከበሮ ክፍል ምሳሌያዊ ትርጉም
አለው ምሳሌውን ግልጽ ለማድረግ የሚከተለውን ስዕላዊ መግለጫ እንመለከት እና ወደ ትንታኔው እንሂድ።
ከበሮ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ግራና ቀኝ ሲመታ ስንመለከልት ጌታችን በአይሁድ እጅ በጥፊ መመታቱን ያስታውሰናል።
፩. ሰፊው የከበሮው አፍ
የመለኮት ምሳሌ ነው።ይህ የከበሮ አፍ የጌታችንን የባህሪ አምላክነት ምሉዕ በኵለሄ መሆኑን አስልጣኑ ወሰን ድንበር እንደሌለው

የሚያስታውሰን ነው::የ አፉን መስፋት ስንመለከት በ አጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ በህልውና በመለኮት ባሕርይ አባቱ ከአብ ባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተስተካከለ ሁሉን የያዘ ሁሉን የሚገዛ መሆኑን እናስባለን::

፪. ጠባቡ የከበሮው አፍ

የትስብእት ምሳሌ ነው በመዝሙር ጊዜ እየተቁረቁረ ድምጽ የሚሰጠው ጠባቡ የከበሮ አፍ የወልድ እግዚአብሔርን በጠባብ ደረት በ አጭር ቁመት ተወስኖ መገለጥ የሚያመለክተን ነው::ፍጥረታትን ሁሉ የሚገዛ እሱ በስልጣኑ ሽረት በመለኮቱ ኅልፈት የሌለበት

ቢሆንም ስጋን ተዋህዶ ተገልጧል።ይህንን ጠባብ የከበሮ አፍ ስንመለከት ሁሉን የሚገዛ እሱ በ አጭር ቁመት በጠባብ ደረት መወሰኑን እናስባለን። ዩሐ፧፩፡፩-፲፬

፫. ከበሮው የሚለብሰው ጨርቅ

ከበሮ የጌታችን ምሳሌ እንደሆነ ከላይ አይተናል። ከዚህ አንጻር የለበሰው ጨርቅ ደግሞ በዕለተ ዓርብ አይሁድ ጌታችንን ያለበሱት ጨርቅ (ቀይ ከለሜዳ)ምሳሌ ነው። ’’ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ አለበሱት’’ ማቴ 26:28

፬. በከበሮው ላይ የተለጠፈው ጠፍር

በጌታችን ጀርባ ላይ የታየው የግርፋት ሰንበር ምሳሌ ነው።

ጠፍሩን በከበሮው ላይ ስንመለከት በጌታችን ጀርባ ላይ የታየውን ሰንበር እናስታውሳለን።
"እጆቼን እና እግሮቼን ቸነከሩኝ አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ" መዝ 21(22):16 እንዲል ጌታችን አጥንቱ እስኪቆጠር ጀርባው እስኪቆስል ተገርፏልና የዚያ ምሳሌ ነው።
፭. የከበሮው ማንገቻ
የከበሮውን መምታት ስናስብ በ አንገታችን የምናስገባው ማንገቻ ጌታችንን አስረው የጎተቱበት ገመድ ምሳሌ ነው። አይሁድ ጌታችንን ወደ ቀራኒዮ ሲወስዱት የእጁ መጋፊያና መጋፊያ እስኪገጥም ድረስ በገመድ የእንግርግሪት

አስረው ጎትተውታል መንገቻውን ከበሮው ላይ ስናይ ይኽንን ጌታችን የታሰረበትን ገመድ እናስታውሳለን።

የከበሮ አመታት፦ ከበሮ ሲመታ ቀጥ ተብሎ አይመታም፤ መዘምራን ግራና ቀኝ እያሸበሸቡ ይመታሉ ይህም ጌታ ከሐና ቀያፋ ፤ ከቀያፋ ወደ ጲላጦስ ያደረገውን እንግልት ያስታውሰናል።* ከበሮ መጀመሪያ በርጋታ ይመታና በፍጥነት ይዘዋወራል ይህም ጌታችንን አይሁድ እንደያዙት መጀመሪያ በቀስታ እየዘበቱ ይመቱት ነበር፤ በኋላ ግን ጲላጦስ

ተመራምሮ ነፃ ሳያወጣው የሰንበት ቀንም ሳይገባብን ኑ እንደብድበው የማለታቸው ምሳሌ ነው፡፡ በማሕሌት ላይ ከበሮው መሬት ላይ ተቀምጦ ሲመታ ጌታችን መሬት ላይ ወድቆ መንገላታቱን እናስባለን፡፡የከበሮ 2 ክፍሎች፦ ከበሮ ስታስቀምጡ ሁልጊዜ ሰፊው አፍ ወደ ላይ መሆን አለበት፤ ትንሹን ክፍል ወደ ላይ ካስቀመጥን ግን ስህተት ነው፡፡ ሰፊው የከበሮ ክፍል የመለኮት ምሳሌ ነው፤ ይህም የጌታችንን የባህርይ አምላክነትና ምሉዕ በኹለሄ መሆኑን ለሥላጣኑ ወሰን ድንበር እንደሌለው የሚያስታውሰን ነው፡፡ ጠባቡ የከበሮ ክፍል ደግሞ የትስብእት ምሳሌ

ነው፤ ይህም ጌታችን በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት ተወስኖ ሥጋን ተዋህዶ መገለጡንና የዮሐንስ ወንጌልን ያስታውሰናል፦*በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ “ቃልም እግዚአብሔር ነበረ … ቃልም ሥጋ ሆነ” [ዮሐ. 1-14]ከበሮ የሚለብሰው ልብስ አይሁድ ጌታን ያለበሱት የቀይ ከለሜዳ ምሳሌ ነው። በከበሮው ላይ የተጠላለፈው ጠፈር በጌታችን ጀርባ ላይ የታየው የግርፋት ሰንበር ምሳሌ ነው። የከበሮው ማንገቻ አይሁድ ጌታን የጎተቱበት ገመድ ምሳሌ ነው።ቤተክርስቲያን ከጣራዋ እስከ መሬቷ ሁሉም ሥርዓቷ

ያስተምራል ፤ ባህረ ጥበብ ቤተክርስቲያን እየተናገረች ታስተምራለች ሳትናገር ዝም ብላም ታስተምራለችና!! ወስብኃት ለእግዚአብሔር

Miko ZE Ethiopia
መብራት ለምን እናበራለን?
1. የብርሃን መላእክት ምሳሌ ስለሆነ ነው፡፡
2ኛ ቆሮ.11 ÷14
ይህም፡ድንቅ፡አይደለም፤ሰይጣን፡ራሱ፡የብርሃንን፡መልአክ፡እንዲመስል፡ራሱን፡
ይለውጣልና፡፡
2. የቅዱሳን ምሳሌ ነው፡፡

ማቴ.5÷14-18
እናንተ፡የዓለም፡ብርሃን፡ናችኹ፡፡በተራ
ራ፡ላይ፡ያለች፡ከተማ፡ልትሰወር፡አይቻ
ላትም፡፡
መብራትንም፡አብርተው፡ከእንቅብ፡በ
ታች፡አይደለም፡እ
ንጂ፡በመቅረዙ፡ላይ፡ያኖሩታል፡በቤት፡
ላሉት፡ኹሉም፡
ያበራል፡፡
መልካሙን፡ሥራችኹን፡አይተው፡በሰ
ማያት፡ያለውን፡አባታችኹን፡እንዲያከ
ብሩ፡ብርሃናችኹ፡እንዲሁ፡በሰው፡ፊት
፡ይብራ፡፡ እኔ፡ሕግንና፡ነቢያትን፡ለ
መሻር፡የመጣኹ፡አይምሰላችኹ፤ልፈ
ጽም፡እንጂ፡ለመሻር፡አልመጣኹም፡፡እ
ውነት፡እላችኋለኹ÷ሰማይና፡ምድር፡እ
ስኪያልፍ፡ድረስ÷ከሕግ፡አንዲት፡የው

ጣ፡ወይም፡አንዲት፡ነጥብ፡ከቶ፡አታል
ፍም፥ኹሉ፡እስኪፈጸም፡ድረስ።
ዮሐ. 5÷35
ጌታ ስለ ዮሐንስ የተናገረው
እርሱ፡የሚነድና፡የሚያበራ፡መብራት፡
ነበረ፥እናንተም፡ጥቂት፡ዘመን፡በብርሃ
ኑ፡ደስ፡ሊላችኹ፡
ወደዳችኹ።
3. እግዚአብሔር አምላካችን እራሱ ብርሃን ነው።
ዮሐ.1÷5
ብርሃንም፡በጨለማ፡ይበራል፥ጨለማ
ም፡አላሸነፈውም።
4. እግር በብርሃን እንደሚመራ ሁሉ እኛም በእግዚአብሔር ሕግ እንደምንመራ ለመግለጽ ነው።
መዝ. 118 ÷ 105

ሕግኽ፡ለእግሬ፡መብራት፥ለመንገዴ፡ብ
ርሃን፡ነው።
5. ብርሃን ስናበራ ክርስቶስን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን ያሳያል።
ማቴ. 25 ÷ 1-30
በዚያን፡ጊዜ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡መ
ብራታቸውን፡ይዘው
፡ሙሽራውን፡ሊቀበሉ፡የወጡ፡ዐሥር፡
ቈነግዥርትን፡ትመስላለች።
ከነርሱም፡ዐምስቱ፡ሰነፎች፡ዐምስቱም፡
ልባሞች፡ነበሩ።
ሰነፎቹ፡መብራታቸውን፡ይዘው፡ከነር
ሱ፡ጋራ፡ዘይት፡አ
ልያዙምና፤..............................

..................................................

6. በዘመነ ሐዋርያት መብራት፣

ጢፍ ይቀጣጠል ነበር፡፡
ሐዋ. 20 ÷ 8
ተሰብስበንም፡በነበርንበት፡ሰገነት፡እጅ
ግ፡መብራት፡
ነበረ፡፡
7. እግዚአብሔርም መብራት
በምኩራብ እንዲያበሩ አዟል
ዘሌ. 24 ÷ 1-4
እግዚአብሔርም፡ሙሴን፡እንዲህ፡ብሎ
፡ተናገረው፦
መብራቱን፡ኹል፡ጊዜ፡እንድታበራበት
፡ለመብራት፡ጥሩ፡
ተወቅጦ፡የተጠለለ፡የወይራ፡ዘይት፡ያ
መጡልኽ፡
ዘንድ፡የእስራኤልን፡ልጆች፡እዘዛቸው፡፡
3፤በምስክሩ፡
መጋረጃ፡ውጭ፡በመገናኛው፡ድንኳን፡

ውስጥ፡አሮን፡ከማ
ታ፡እስከ፡ማለዳ፡ድረስ፡
በእግዚአብሔር፡ፊት፡ኹል፡ጊዜ፡ያሰና
ዳው፤ለዘለዓለም፡ለልጅ፡ልጃቸኹ፡ሥ
ርዐት፡ይኹን።
በእግዚአብሔር፡ፊት፡በጥሩ፡መቅረዝ፡
ላይ፡መብራቶቹን፡ኹል፡ጊዜ፡ያሰናዳቸ
ው።

Kok'eb Hadgu
ማስጠንቀቂያ :-☛☛አንብበሽ ካልጨረሽው አትጀምሪው።☚☚
like እና Comment ከማድረግ አንብበሽ ለሌሎች share አድርጊ።
በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

፩ አምላክ አሜን።
☞☞⁜⁜⁜ክርስቲያናዊ
አለባበስ⁜⁜⁜☜☜
☛☛"ሴት የወንድን ልብስ አትልበስ ወንድም የሴትን ልብስ አይልበስ ይህን የሚያደርግ በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው።" (ዘዳ. 22:5)☚☚
ስለ አለባበሳችን እንወያያለን ዛሬም እህቶቻችን ላይ እናተኩራለን ምነው እኛ ላይ ብቻ እንደማትሉኝ ተስፋ አለኝ።
ስለ አለባበስ መነጋገር ያስፈለገን እውነተኛ ክርስቲያን በአነጋገሩ፣ በአረማመዱ፣
በአመጋገቡ፣ በአለባበሱ፣ ብቻ በሁሉ ነገሩ የተለየ መሆን ስላለበት

ነው:: ይኸውም ሁሉን
በአግባብና በሥርዓት ስለማድረግ
ነው እህቶቻችን ላይ ማተኮር
ያስፈለገው ደግሞ፦
በአብዛኛው በዚህ ረገድ ትችት
የሚበዛው እነሱ ላይ ስለሆነ ነው::
እነሆ ውድድሩ ከዕለት ወደ ዕለት
እየጨመረና እየከፋ ነው ለመልካም
ነገር መወዳደር
ባልከፋ ነገር ግን በከተማችን
በተለይም በዋና ዋና መንገዶች ላይ
የምናየው
የእህቶቻችን አለባበስ አንዷ ከሌላዋ
ልቃና በልጣ ለመታየት የሚደረግ
ግብግብ
እንደሆነ መገመት አያዳግትም::
በእርግጥ እህቶቻችን በዚህ

እንደማይስማሙ እናውቃለን አብዛኞቹም ስለተመቸኝና የምወደው
አይነት አለባበስ ስለሆነ ነው እንዲህ የምለብሰው ይሉናል ይሁን እንጂ እውነታው ሌላ ይመስላል ምክንያቱም:-
* ብርድ ልብስ ለብሰን እንኳን በማንቋቋመው የብርድ ወቅት ሰውነትን በቅጡ
የማይሸፍን ብጣሽ ጨርቅ ጣል አድርጎ መውጣት እንዴት ያለ ምቾት ነው?
*እጅግ አስጨናቂ ሙቀት ባለበት ሰዓት ሰውነት ላይ ተጣብቆ ሌላ ጭንቀት የሚፈጥር
አለባበስ እንደምን ብሎ ያስደስታል?

ዓላማችን ምንም ይሁን እሱ ላይ የመከራከር ፍላጎት የለንም ነገር ግን አለባበሳችንን
እንደ ክርስቲያን እንፈትሸው ዘንድ ይገባልና ይህ ተግፈ
መሰልጠን ወይስ መሰይጠን?
አብዛኞቹ ሴቶች ይህን ተግባር ስልጣኔ እንጂ ስህተት ነው ብለው አያምኑም፡፡ ለነዚህ
ሴቶች ከኃይማኖት ብቻ ሳይሆን ከባህላችን ጭምር ያፈነገጠውን የምዕራባውያን
አለባበስ መልበስ ዘመናዊነት ነው፡፡ ☛ላንቺስ?☚ መጽሐፍ ቅዱስስ ምን ይላል?
------------------------------
-----------//////////////////////////

----------------

--------------------

ማንኛዋም ሴት የሰውነቷን ቅርፅ የሚያሳይ ወይም ክፍትፍት ልብስ ለብሳ መሄዷ
የሁሉንም ወንዶች ስሜት መፈታተኗ እርግጥ ከመሆኑም በላይ በመንፈሳዊ ህይወት
ደካማ የሆኑትን ደግሞ ለኃጢያት አጋልጦ ይሰጣል፡፡ እዚህ ላይ የተሳሳተው በራሱ
ደካማነት ነው ብሎ ምክንያት መስጠት አይቻልም እግዚአብሔር የሚጠይቀው በማን
ተሰናከለ የሚለውን ጭምር ነውና በክርስትና ደግሞ ሰውን ማሰናከል እጅግ የከፋ ኃጢያት ነው፡-

☛☛"ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ
ባህር መስጠም ይሻለው ነበር፡፡" (ማቴ. 18፡6)☚☚

አንዳንድ ሴቶች እግዚአብሔር ምን ሰራሽ እንጂ ምን ለበስሽ አይለኝም ይላሉ

እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል፦

☛☛"እንግዳ ልብስ የሚለብሱትንም ሁሉ እቀጣለው፡፡" (ትን.ሶፎ. 1፡18) ☚☚

እንግዲህ የሴቶቹን እንቀበል ወይስ የእግዚአብሔርን ምርጫው ያንቺው ነው እህቴ

መጽሐፍ ግን እንዲህ ይላል፡-

☛☛"ከስው ይልቅ ለእግዚአብሔር

ልንታዘዝ ይገባል፡፡”
(የሐዋ. 5፡29)☚☚
በሴቶችና በወንዶች መካከል የአለባበስ ልዩነት ሊኖር ይገባል
☛☛“ሴት የወንድን ልብስ አትልበስ ወንድም የሴትን ልብስ አይልበስ ይህን የሚያደርግ በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው፡፡” (ዘዳ. 22፡5)☚☚
ታዲያ ቀሚስን የወንድ ሱሪን የሴት ማን አደረገው? ይህ የሰነፍና ለስህተታቸው ምክንያትን የሚሹ ሴቶች የሚያነሱት ጥያቄ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እኛ ኦርቶዶክሳውያን የእግዚአብሔርን ቃል አውቀን ልንፈፅመው እንጂ

በቃሉ ላይ
የምንፍቅና ጥያቄ እናነሳ ዘንድ
ተገቢ አይደለም ግን ደግሞ
ተፈጥሯችንን ብቻ በማየት
ህሊናችን እራሱ ቢናገር ሱሪ የሴት
ነውን? ቀሚስስ የወንድ ነው እንዴ
☛☛“ተፈጥሮ እንኳን
አያስተምራችሁምን?
(1ኛ ቆሮ. 11፡14)☚☚
☛☛“ዳሩ ግን ማንም ሊከራከር
ቢፈቅድ እኛ ወይም የእግዚአብሔር
አብያተ ክርስቲያናት
እንዲህ ያለ ልማድ የለንም፡፡” (1ኛ.
ቆሮ. 11፡16)☚☚
ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ስህተት
መሆኑን መናገር እንጂ መከራከር
አያስፈልግም

ክርስትና በምርጫ ነውና፡፡
☛☛“በፊትህ እሳትና ውሃን አኑሬአለው ወደ ወደድከው እጅህ ክተት፡፡” (ሲራ. 15፡15)☚☚
እዚህ ላይ ግን ቀሚስ ሲባል ከውስጥ ሱሪ የማይሻለውን ብጣሽ ጨርቅ እንዲሁም
ቁመቱ ረዥምም ሆኖ ከሰውነት ጋር የሚጣበቀውን አይነት አለባበስ ማለት እንዳልሆነ ልብ
እንበል፡፡
እህቶቻችን ሆይ ማስተዋልን ትላበሱ ዘንድ እንለምናችኋለን መሰልጠንና መሰይጠንም
ትለዩ ዘንድ ይሁን ሰውነትሽ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነውና ሁሉን በአግባብና

በሥርዓት አድርጊለት፡፡
ደግሞም ክርስትና ራስ ወዳድነትን አብዝታ ትጠላለች ምንም ነገር ስናደርግ ስለ ሌላው
ሰው ልናስብ ያስፈልገናል እኛስ ሰውን ወደ ዝሙት ሊያመራው ስለሚችል አለባበሳችን
እጅግ ተጨነቅን ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ ወንድማችንን ስለማሰናከል ምን አለ
☛☛“መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ ወንድሜን እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ
ሥጋ አልበላም፡፡” (1ኛ.ቆሮ 8፡13) ☚☚
እንግዲህ ክርስትና እዚህ ድረስ ነው ስለራሳችን ብቻ ሳይሆን ስለ

ወንድሞችና
እህቶቻችን የምናስብባት ለእነሱም መሰናከያ እንዳንሆን እየተጠነቀቅን ሁሉን
በአግባብና በሥርዓት የምናደርግባት፤ እምነታችንን በምግባር የምንገልጽባት ናት፡፡
☛☛"በእውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዝንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን፡፡
(ትን.ኤር. 13፡27)☚☚
እህቴ ሆይ አንቺም ኤርሚያስ እንዳለው ኢትዮጵያዊነትሽን ጠብቂ የምዕራባውያን በዓል
ከሆነው አለባበስም ሆነ የምንዝር ጌጥ ራስሽን አርቀሽ በሚያኮራው ኢትዮጵያዊ

ባህላችን ትዋቢ ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳሽ።

እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ ስለእውነት አሁን ማን ነው ተጠያቂ የጡት ካንሰር ቢይዘን??

አረ እነዲያው ለመሆኑ ስንቶቻችን የጡት ካነሰር፣ የዲስክ መንሸራተት፣ የማህፀን ካንሰር እንዲሁም ሌሎች የበሽታ ጠንቆች የሚመጡብን በዚህ አለባበሳችን በመበላታችን እንደሆን አስበነው እናውቅ ይሆን??

እስኪ በአሁኑ ዘመን ከጤነኛው አወላለድ (normal birthing) ውጭ የሚወልዱ እናቶች ብዛት ስንት ፐርሰንት እንደሆነ አገናዝበን እናቅ ይሆን ይህስ በምን የመጣ መሆኑን

አስበን እናቅ ይሆን?? ብዙዎቹ እኮ በኦፕራሲዮን እንጅ በማርያም ምልጃና ፀሎት በመልዓኩ ቅዱስ ሩፋዔል ጥበቃ ሲገላገሉ አይታዩም፡፡ ወደድንም ጠላንም ይህ የዚህ የአለባበሳችን የእርግማን ውጤት ነው ከተሳሳትሁ አርሙኝ እንጅ አትርገሙኝ፡፡
እግዚአብሔር ለሁላችንም አስተዋይ ልቦና ይስጠን፡፡ አሜን!!!!
ሁላችን ምግባር ያለው እምነት እንዲኖረን እግዚአብሔር ይርዳን፡፡ አሜን!!!
ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የቀደመችው ቀጥተኛይቱ ጠባቢቱ እውነተኛይቱ መንገድ ለዘላለም ኑሪልን፡፡፡፡

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት መልስ አላት

መቁዋሚያ

---

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን !

መቁዋሚያ ምሳሌነቱ :-ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሸከመውና የተሰቀለበት ቅዱስ መስቀል ምሳሌ ነው ።

በሥርዓተ ማህሌት ጊዜ መዘምራኑ መጀመሪያ መቁዋሚያቸውን ከላይ ወደ ታች ያደርጉታል ።

ይህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት

መውረዱን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሱዋ ነፍስ ነስቶ መወለዱን ያመለክታል ከዚያም ዓለምን ዞሮ ማስተማሩን ለማጠየቅ መቁዋሚያውን ከግራ ወደ ቀኝ ያሽከረክሩታል ።

መዘምራኑ መቁዋሚያቸውን ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ የሚያደርጉት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐና ቀያፋ ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ መመላለሱን መከራ መቀበሉን ለማሳሰብ ነው ።

መቁዋሚያውን ወደ መሬት የሚደስቁት የማይሞት ጌታ ወደ መቃብር ወረደ ሲሉ ነው ። ወደ መሬት የደሰቁትን መልሰው ወደ

ላይ ማንሳታቸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ መነሳቱን ለመመስከር ነው ::

በተመሳሳይ ሁኔታ ከቀድሞ በበለጠ ከፍ አድርገው በኃላ ረጋ ብለው የሚመልሱት ዕርገቱንና ዳግም ምፅዓቱን ለማዘከር ነው :: ሞቶ የተነሳው ተነስቶም ያረገው ዳግመኛ ይመጣል ሲሉ ነው ::

የአብ ጸጋ የወልድ ቸርነት የመንፈስ ቅዱስ አንድነት የእመቤታችን አማላጅነት የቅዱሳን መላእክት ፈጣን ተራዳዒነት ጥበቃቸው የፃድቃን ሰማዕታት የቅዱሳን ሐዋሪያት የአበው መነኮሳት ምልጃ ጸሎት ቃል

ኪዳናቸው ረድኤት በረከታቸው ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን አሜን አሜን !!!

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት መልስ አላት
ከበሮ ለምን ይጮሀል ???
*********************

የኔታ ለተማሪዎቹ አንድ ጥያቄ አቀረቡ
.......ልጆች ከበሮ ለምን ይጮሀል ???
...የኔታ በቆዳ ስለተወጥረ ነው አለ አንድ ተማሪ የዳዊት መሀደሩን በጁ አንጠልጥሎ ለመመለስ እየቸኮለ...

የኔታም አይደለም አሉ ነጭ ሪዛቸውን ወደታች እየጎተቱ

ሌላኛው ተማሪም .... የኔታ ከእንጨት ስለተሰራ ነው አለ የለበሰውን ለምድ ከፍ ከፍ እያደረገ... የኔታም ትንሽ ዝም ካሉ በኋላ .. አይደለም አሉ ... ተማሪው ሁሉ ማውጣት ማውረድ ጀመረ በሀሳብ ተወጣጠረ ..ሁሉም የመጣለትን እና የገመተውን መናገር ቀጠለ ግን የሚመልስ ጠፋ ..... አንድ የሁሉንም ምላሽ በእርጋታ ይሰማ የነበረ ተማሪ እጁን አወጣ .... እሽ ልጄ አሉት የኔታ ....ድምፁን ከፍ አደረገና የኔታ እድሉን ስለሰጡኝ አመሰግናለሁ ብሎ እጅ ከነሳ በኋላ

.....የኔታ ከበሮ የሚጮኸው... "ባዶ ስለሆነ" ነው አለ...
የኔታም የልጁን ምላሽ በማድነቅ ከወንበራቸው በመነሳት ልጄ ተባረክ ተማሪዎቹም በጭብጨባ አጀቡት ...
... የኔታም ቀጠል አደረጉና ....ልጆች " ባዶ "የሆነ ነገር ሁሉ ይጮሀል በውስጡ የሆነ ነገር ያለው እቃ ግን አይጮኸም...የተማረም ሰው እንዲሁ ነው ... እውቀት ያለው አይጮኸም ... የተማረ አይጮኸም ... ጥበብ ያለው አይጮኸም ...ምንጊዜም ባዶ የሆነ ሰው ሲጮህ ... ጥበብ የሌለው ሲፎክር ... እውቀት የሌለው

ሲያቅራራ
ይታያል ... እና ልጆቼ እናንተ
"ባዶ "እንዳትሆኑ
እውቀትን ጨምሩ ... በእውቀት
ላይ ጥበብን ... በጥበብ ላይ
እግዚአብሔርን መፍራት
ጨምሩ.....ምድራችንን በማስተማር
እና በመስበክ የሞሉ ግን " ባዶ"
የሆኑ ...
ምድሪቱን በዝማሬ የሞሉ
በሀይማኖት እና ምግባር ግን "ባዶ"
የሆኑ...ጌታ ሆይ..ጌታ ሆይ የሚሉ
ግን ጌታ የማያውቃቸው እንደ ሰው
ተፈጥረው እንደ እንሰሳ በደመ
ነፍስ የሚኖሩ ሰዎች በዝተዋልና
እናንተ ግን ማንም እንዳያስታችሁ
ተጠንቀቁ .... ማቴ 24፥-4... ብለው

የኔታ ቁጭ አሉ ተማሪዎቹም የኔታን አመስግነው ትምህርታቸውን ቀጠሉ

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት መልስ አላት

የከበሮ ክፍል ምሳሌያዊ ትርጉም

የከበሮ ክፍል ምሳሌያዊ ትርጉም አለው ምሳሌውን ግልጽ ለማድረግ የሚከተለውን ስዕላዊ መግለጫ እንመለከት እና ወደ ትንታኔው እንሂድ።

ከበሮ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ግራና ቀኝ ሲመታ ስንመለከት

ጌታችን በአይሁድ እጅ በጥፊ መመታቱን ያስታውሰናል።

፩. ሰፊው የከበሮው አፍ

የመለኮት ምሳሌ ነው።ይህ የከበሮ አፍ የጌታችንን የባህሪ አምላክነት ምሉዕ በኵለሄ መሆኑን አስልጣኑ ወሰን ድንበር እንደሌለው የሚያስታውሰን ነው።የ አፉን መስፋት ስንመለከት በ አጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ በህልውና በመለኮት ባሕርይ አባቱ ከአብ ባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተስተካከለ ሁሉን የያዘ ሁሉን የሚገዛ መሆኑን እናስባለን።

፪. ጠባቡ የከበሮው አፍ

የትስብእት ምሳሌ ነው በመዝሙር

ጊዜ እየተቁረቁረ ድምጽ የሚሰጠው ጠባቡ የከበሮ አፍ የወልድ እግዚአብሔርን በጠባብ ደረት በ አጭር ቁመት ተወስኖ መገለጥ የሚያመለክተን ነው።ፍጥረታትን ሁሉ የሚገዛ እሱ በስልጣኑ ሽረት በመለኮቱ ኅልፈት የሌለበት ቢሆንም ስጋን ተዋህዶ ተገልጧል።ይህንን ጠባብ የከበሮ አፍ ስንመለከት ሁሉን የሚገዛ እሱ በ አጭር ቁመት በጠባብ ደረት መወሰኑን እናስባለን። ዩሐ፤፩፡፩-፩፬

፫. ከበሮው የሚለብሰው ጨርቅ

ከበሮ የጌታችን ምሳሌ እንደሆነ ከላይ አይተናል። ከዚህ አንጻር የለበሰው ጨርቅ ደግሞ በዕለተ ዓርብ አይሁድ ጌታችንን ያለበሱት

ጨርቅ (ቀይ ከለሜዳ)ምሳሌ ነው፡፡
’’ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ
አለበሱት’’ ማቴ 26:28
፲. በከበሮው ላይ የተለጠፈው
ጠፍር
በጌታችን ጀርባ ላይ የታየው
የግርፋት ሰንበር ምሳሌ ነው፡፡
ጠፍሩን በከበሮው ላይ ስንመለከት
በጌታችን ጀርባ ላይ የታየውን
ሰንበር እናስታውሳለን፡፡
’’እጆቼን እና እግሮቼን ቸነከሩኝ
አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ’’ መዝ
21(22):16 እንዲል ጌታችን
አጥንቱ እስኪቆጠር ጀርባው
እስኪቆስል ተገርፏልና የዚያ ምሳሌ
ነው፡፡
፲፩. የከበሮው ማንገቻ

የከበሮውን መምታት ስናስብ በ አንገታችን የምናስገባው ማንገቻ ጌታችንን አስረው የጎተቱበት ገመድ ምሳሌ ነው። አይሁድ ጌታችንን ወደ ቀራኒዮ ሲወስዱት የእጁ መጋፊያና መጋፊያ እስኪገጥም ድረስ በገመድ የእንግርግሪት አስረው ጎትተውታል መንገቻውን ከበሮው ላይ ስናይ ይኽንን ጌታችን የታሰረበትን ገመድ እናስታውሳለን።

ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

ጧፍ

፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨

ካህኑ ወንጌል ሲያነብ ጧፍ

ይይዛል; አልጨለመ ብርሐን አለ ለምንድን ነው ቢሉ ልበ አምላክዳዊት “ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሐን ነው” ስለሚል ነው። (መዝ 119 :105) ወንጌሉ ነውና የሚነበበው ወንጌሉም ለእግራችን መብራት ለመንገዳችንም ብርሃን ስለሆነ ነው።

አንድም ክቡር ዳዊት እንዲህ ብሏል፦ “ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው” (መዝ. 119፥105)። ልበአምላክ ዳዊት ይህን ያለበት የራሱ ታሪክ አለው፦በመካከለኛው ምሥራቅ ከቀኑ ሐሩር የተነሣ በሌሊት መጓዝ የተለመደ ነው። ከጨለማውም ጋር

ሽፍቶችና ዘራፊዎች አሳሳቢዎች ስለሆኑ በኅብረት መጓዝ የተለመደ ነው። ጨለማው ጥልቅ መልክአ ምድሩም ገደላማ በመሆኑ የሚረግጡትን በትክክል ለማየት ይቸገራሉ። ሜዳ የረገጡ መስሎአቸው ገደል ሊገቡ ይችላሉ። የሚረግጡትን እርምጃ በትክክል ለማየት እግራቸው ላይ መብራት አስረው ይሄዱ ነበር። ይህ የሚረግጡትን በትክክል ያሳያል። ነቢዩ በዚህ ምሳሌ፡- "ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው" አለ። ለዚህም ነው ወንጌሉ ሲነበብ ጧፍ የሚያዘው። ሕጉ ለእግራችን መብራትነውና! አንድም በቤተክርስቲያን ውስጥ በብዛት ሻማ

አለ; ይህም እግዚአብሔር በባሕርይው ብርሐን ስለሆነ ነው ፤ ሻማውእየቀለጠ ብርሃን ይሰጣል ይህም ቅዱሳኑ ስለቤተክርስቲያን እንደሻማ እየቀለጡ ለዓለም ብርሐን የመሆናቸው ምሳሌ ነው፡፡

Mekane Selam St. Urael– with ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

ዕጣን

፨፨፨፨

የእጣን ዛፍ የሚገኘው በበረሀ ነው የቤተ መቅደሥ አገልግሎት ከተጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የፀሎት ማሣረግያ መስዋእት ሆኖ በካህናት

ይቀርባል (ኦ.ዘፅአት 30:1) (ኦ.ዘሌዋውያን 16:12-13)

-----

፨፨ ዕጣን የጌታችን ምሣሌ ነው ፨፨

ሰብአ ሠገል ዕጣን አምሀ አድርገው የሰጡትም እንደ እጣን ትሰዋልናለህ ሢሉ ነው (ማቴ 2:11) ። ዕጣን ለሠው ልጆች ሀጥያት እንደሚሠዋ ጌታችንም ሥለ ሠው ልጆች ሁሉ ራሡን ለሞት አሳልፎ ሰጥቷል ።

----

፨፨ ዕጣን የቤተክርሥትያን ምሣሌ ነው ፨፨

<< መአዛዋም እንደ ከርቤና ዕጣን የሆነችው ከልዩ ከነጋዴ ቅመም ሁሉ የሆነችው ይህች ከምድረ በዳ

እንደ ጢስ ምሠሶ የወጣችው ማን ናት? >> ሲል በምድረ በዳ ከተመሰለችው አለም ተለይታ ወደ ሠማይ ንጉሥ ወደ እግዚአብሄር የምትዘረጋ ጸሎቷም የሚሠማላት ቤተክርስትያንን በእጣን መሥሏታል (መኃልዬ ዘሠለሞን 3:6) ፡፡

-----

፨፨ ዕጣን የምእመን ምሣሌ ነው ፨፨

ቅዱስ ጳውሎስ

" በሚድኑትና በሚጠፉት ዘንድ ለእግዚአብሄር የክርስቶስ መአዛ ነንና ለእነዚህ ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ ለእነዚያም ለህይወት የሚሆን የህይወት ሽታ ነን "

እንዳለ (2ኛ ቆሮ 2:15-16) ፡፡ እጣን በተሠዋ ቁጥር ወደላይ እንደሚወጣ የክርሥትያኖችም ህይወት ከክብር ወደ ክብር ወደ ሠማያዊ ማእረግ ትሄዳለችና ፡፡

-----

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ደግሞ እጣንና ንጹህ ቁርባን (ሥጋ ወደሙ) ከፀሀይ መውጫ እሥከ ፀሀይ መግቢያ ድረሥ ለእግዚአብሄር ሥም እንደሚቀርብ (እንደሚሠዋ) ነቢዩ ሚልክያሥ ተናግሯል (ት.ሚልክያሥ 1:11) ቅድሥት ቤተክርሥትያንም ሥትፈፅመው ትኖራለች ፡፡

መልአኩ ቅዱሥ ገብርኤልም ካህኑን ዘካርያሥን ልጅ

እንደሚወልድ ሊያበሥረው ወደ መቅደሶ በገባ ግዜ ካህኑን ያገኘው እጣን ሲያጥን ነበር (ሉቃሶ 1:10) ::

የእጣን መሥዋእት በምድር ላለነው ቀርቶ በሠማይም ቢሆን ለእግዚአብሄር ይቀርባል (ዮ.ራዕይ 5:8 እንዲሁም ዮ.ራዕይ 8:3-4) :: ስለዚህ የዕጣን መሥዋእት በሀዲሶ ኪዳንም አልራተቋረጠምና እናት ቤተክርሥትያናችን ተግባራዊ ታደርገዋለች ::::

ወስብሀት ለእግዚአብሄር

ምንጭ: ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

**ይድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ**

***ከበሮ ለምን ይጮሀል?***

***የኔታ ለተማሪዎቻቸው አንድ ጥያቄ አቀረቡ..... "ልጆችከበሮ ለምን ይጮሀል?"***

**የኔታ ....የኔታ .... "በቆዳ ስለተወጠረ ነው"......አለአንድ ተማሪ**

**የዳዊት መሀደሩን በእጁ አንጠልጥሎ ለመመለስ እየቸኮለ። የኔታም "አይደለም አሉ" ሌላኛው ተማሪም...."የኔታ ከእንጨት ስለ ተሰራ ነው" አለ የለበሰውን ለምድ ከፍ ከፍ እያደረገ ........የኔታም ትንሽ ዝም ካሉ በኋላ ..... "አይደለም አሉ"...ተማሪው ሁሳ ማውጣት**

ማውረድ ጀመረ
በሀሳብተወጠረ:: ሁሉም
የመጣለትን እና የገመተውን
መናገር
ቀጠለግን የሚመልስ ጠፋ::አንድ
የሁሉንም ምላሽ በእርጋታ
ይሰማ የነበረተማሪ እጁን
አወጣ::...." እሽ ልጄ " አሉ የኔታ
.....ድምፁን ከፍ አደረገና ....,የኔታ
እድሉን ስለ ሰጡኝ
አመሰግናለሁ ብሎ እጅ ከነሳ
በኋላ ....የኔታ ከበሮየሚጮኸው
"ባዶ ስለሆነ ነው"! አለ::የኔታም
የልጁን ምላሽ በማድነቅ
ከወንበራቸው በመነሳት ...ልጄ
ተባረክ አሉ::ተማሪዎቹም
በጭብጨባ አጀቡት::የኔታም ቀጠል

አደረጉና ..... ልጆች "ባዶ" የሆነ ነገር ሁሳ ይጮሀል በውስጡ የሆነ ነገር ያለው እቃ ግን አይጮህም።የተማረም ሰው እንዲሁ ነው። እውቀት ያለው አይጮህም፣ ጥበብ ያለው አይጮህም፣ ምንጊዜም ባዶ የሆነ ሰው ሲጮህ፣ ጥበብ የሌለው ሲፎክር እውቀት የሌለው ሲያቅራራ ይታያል። እና ልጆቼ.... እናንተ "ባዶ" እንዳትሆኑ እውቀትን ጨምሩ፣ በእውቀት ላይ ጥበብን፣ በጥበብ ላይ እግዚአብሔርን መፍራት ጨምሩ።ምድራችንን በማስተማር እና በመስበክ የሞሉ ግን"ባዶ" የሆኑ።

ምድሪቱን በዝማሬ የሞሉ
በሐይማኖትእና በምግባር ግን "ባዶ"
የሆኑ:: ጌታ ሆይ..... ጌታ
ሆይ....የሚሉ ግን
ጌታየማያውቃቸው እንደ ሰው
ተፈጥረው እንደ
እንሰሳ በደመ ነፍስ የሚኖሩ ሰዎች
፣ በዝተዋልና ብለውቁጭ
አሉ::ተማሪዎቹም የኔታን
አመስግነው ትምህርታቸውን
ቀጠሉ::

ማዕተብ: የክርስትናችን ዓርማ ነው
ማህተቤን
አልበጥስም!!!!!! ክፍል ፬

ማዕተብ ያሳሰረ ኦርቶዶክሳዊ
የአባቶቹን የተቀደሰ
ክርስቲያናዊ ትውፊት
እንዳልተቀበለ ያስቆጥረዋል፡፡
በምሳሌያዊ አነጋገርም ሃይማኖት
አልባውን
ማለትም ክርስቲያን ያልኾነውን
ማተብ የለሽ፣
ያልተጠመቀ፣ አረሚ ይሉታል፡፡
ክርስቲያን በማተቡ
መነኵሴ በቆቡ እንዲታወቅ ማተብ
አልባ መኾን
ደግሞ ክርስቲያን ይኹን
ያልተጠመቀ ለመለየት
ያስቸግራል፡፡ በመለዮዋቸው ሌሎች
እንዲታወቁ
ክርስቲያን በማተቡ ክርስትናውን

ሲያሳውቅ ኖሯል፡፡
በተለመደው አነጋገር÷ እገሌ
ማተብ አለው፤
ባለማተብ ነው ሲባል እገሌ ታማኝ
ክርስቲያን
ነው፤ እውነተኛ ሐቀኛ ነው
የማለትን ትርጉም
ይሰጣል፡፡ ባለማተቢቱ ሲባል
ከአሚን ባሏ የረጋች
ከባሏ ሌላ የማታውቅ እውነተኛ
ታማኝ ክርስቲያን
የማለት ፍች አለው፡፡ በዚኽ
ምክንያት በሕዝበ
ክርስቲያኑ ዘንድ የማተብ ትርጉም
ከፍተኛ
ቁምነገርን አዝሎ ይገኛል፡፡
አንዲት ሀገር ነፃና ሉዓላዊ መኾኗ

የሚታወቀው
ወይም ራሷን የቻለች መንግሥት ያላት ከባዕድ
ቀንበር ቅኝ ግዛት ነፃ የወጣች መኾኗ በቀዳሚነት
የሚለየው በባንዴራዋ ምልክትነት እንደኾነ
እንደዚኹም አንድ ክርስቲያን በክርስቶስ አምኖ
በጥምቀት ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነፃ መውጣቱ፣
ነፃነት ያለው አማኝ መኾኑ የሚታወቀው በማተቡ
ምልክት ነው። ለደብዳቤ፣ ለጽሑፍ ዓርማ ማኅተም
ፊርማ እንደሚያስፈልገው ያም ለመተማመኛ

እንደሚያገለግል ጥቅሙ ታውቆ ይሠራበታል።
በዚኹ አንፃር የክርስቲያን ማዕተቡም ሃይማኖታዊ
ጠቀሜታ ይኖረዋል። በቅድሚያ፣ በልቡ
የሚያምነው ሃይማኖት ክርስትናን ሳያፍርበት
በአንገቱ ባለው ማተብ መግለጹ በክርስትናው
አለማፈሩን፣ ክርስትናኽን ካድ ማተብኽን በጥስ
የሚል ዐላዊ ቢመጣና ያን ምልክት አይቶ
ቢሠዋው የሰማዕትነት ክብር ያገኝበታል። ያም
ባይኾን በማተቡ ምልክትነት

በመናፍቃንና
በኢአማንያን የሚቀበለው ዘለፋ ስለ
ክርስቶስ
መስቀል እንደተሸከመ
ያስቆጥረዋል፡፡
ኹለተኛው፣ ያለጥርጥር ክርስቲያን
መኾኑ
ታውቆለት ከክርስቲያን ወገኖች
ጋራ ተሳትፎውን
ማከናወን ይችላል፡፡ ማተብ ከሌለው
ግን
ክርስቲያን ይኹን ያልተጠመቀ
ስለማይታወቅ
በሃይማኖት ዜጎች ዘንድ በቀላሉ
ተቀባይነት
ማግኘት አይችልም፡፡ ሦስተኛ፣
ከማይታወቅበት

አገር እንደወጣ በበሽታም ይኹን በአደጋ ሕይወቱ
ቢያልፍ በማተቡ መታወቂያነት የክርስቲያን ሥርዐት
ተፈጽሞለት በቤተ ክርስቲያን ሊቀበር ይችላል፡፡
አራተኛ፣ ማተብና መስቀል ያለው ክርስቲያን በውኃ
ዋና ወይም በበረሓ ጎዳና በውኃ የሚኖሩ ወይም
በበረሓ ያሉ አጋንንት በቀላሉ ሊለክፉት
አይችሉም፡፡ ይህም በየጠበሉ ስፍራ በተኣምራት
ተረጋግጧል፡፡ አጋንንት የለከፏቸው ሰዎች ማተብና
መስቀል አይወዱም፡፡ የሰፈረባቸው

ርኩስ መንፈስ
ማተብ እንዲበጥሱ መስቀል እንዲጥሉ
ያደርጋቸዋል። ማተብ በሰይጣን ዘንድ ከተጠላ
በአጋንንት ሳለመለከፍ የማዕተቡ መኖር ይጠቅማል
ማለት ነው ።
አንዳንድ ሰዎች የማዕተብ ሥርዐትን ለመቃወምና
ዘመናውያን መስለው ለመታየት ‹‹እምነት በልብ
ነው›› ይላሉ፤ ተሳስተዋል! ሃይማኖት የልብ ብቻ
አይደለም፤ የጠቅላላው ሕዋሳት ኹሉ ናት ።
እግዚአብሔርን ስንወደውና

ስናመልከው በልባችን
ብቻ ሳይኾን በአፋችንም
በአንገታችንም
በጠቅላላው ሰብአዊ ተፈጥሯችን
ኹሉ መኾን
ይገባዋል፤ ምክንያቱም
እግዚአብሔር የጠቅላላው
ሰውነታችን አምላክና ፈጣሪ ስለኾነ
ነው፡፡
‹‹ስለዚኽ በሰው ፊት
የሚመሰክርልኝ ኹሉ እኔ
ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት
እመሰክርለታለኹ፤ በሰው ፊትም
የሚክደኝን ኹሉ
እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ
ፊት
እክደዋለኹ፡፡›› (ማቴ.፲÷፴፪÷፴፫)

በዚኽ ቃለ ወንጌል መሠረት በኢአማንያን ዘንድ ክርስቲያን መኾናችንን የምንገልጸው በልባችን ብቻ ሳይኾን በቃላችንና በሥራችንም ጭምር ነው፡፡ በአንገታችንስ እንዳንመሰክርለት ማን ያግደናል? በአንገታችን ባለው ማዕተብም ለእግዚአብሔር እንመሰክራለን፡፡ የስሙን ምልክት በአንገታችን እናኖራለን፤ አናፍርበትም!! የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ በጥምቀታችን እንደምንመሰክር የጥምቀታችንንም ዓርማ

በማተባችን
እናረጋግጣለን፡፡ (ሮሜ ፲፮÷፲፫፤
ኢዮኤ. ፱÷፴፱፤
ሮሜ ፮÷፩-፫፤ ማቴ.፫÷፲፩-፲፱፤
፩ኛጴጥ.፫÷፳፩-
፳፱፤ ፬÷፲፱-፲፮)
ከወንጌል የተለየች ትምህርት
እንዳንቀበል
ሐዋርያት አስጠንቅቀውናል፡፡
መላእክት በራእይ
ገልጸውልናል፤ ከእግዚአብሔር
አግኝቻለኹ ብለው
የሚመጡትን መናፍስት
እንድንመረምራቸው
በቅዱሳት መጻሕፍት ታዝዘናል፡፡
ማተብ የማሰር
የተቀደሰ ክርስቲያናዊ

ትውፊታችንን የሚቃወሙ
በክርስቶስና ሞትና ትንሣኤ
የማያምኑ ተረፈ
አይሁድ ስለኾኑ ተቃውሞውን ዋጋ
ሳንሰጠው
ማተባችንን እናጠብቃለን፡፡ ‹እንደ
ውሻ
በአንገታችኹ ገመድ አስራችኹ›
ተብለን
በመነቀፋችንም እንደሰትበታለን
እንጂ አንሠቀቅም፡፡
ውሻ ለጌታው ታማኝ ነው፡፡ ሌሎች
የተለከፉ
ያበዱ ዘላን ውሾች እንዳይለክፉትና
ከሞት
እንዳያደርሱት ወይም ወንበዴዎች
በሥጋ መርዝ

ቀብተው ለሥጋው ሲሟሟ
እንዳይገድሉት ትንሽ
ጎጆ ሠርቶለት ቢያስረው ለውሻው
ሕይወት
አስፈላጊ እንደኾነ በኹሉም የታወቀ
ነው፡፡
በዚኹ አንፃር ክርስቲያን ለክርስቶስ
ታማኝ
በመኾኑ በነፍሱ ሞግዚት በቄሱ
እጅ ከሕፃንነቱ
ጀምሮ የድኅነቱ ምልክት በሚኾን
አንገቱ በማዕተበ
ክርስትና ይታሰራል፡፡ ማዕተብ
ጌታችን
መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
በዕለተ ዓርብ ስለ
እኛ ቤዛ ለመኾን የብረት ሀብል

/የብረት ገመድ/
በአንገቱ ታስሮ በአይሁድ መጎተቱን
ስለሚያስታውሰን ለታማኝነታችንና ለክርስቲያንነታችን
ምልክትነቱ ማረጋገጫ ስለኾነ አናፍርበትም።
በድርሳነ ሰንበት ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ የውሻን
ታማኝነት ለክርስቲያን ታማኝነት ምሳሌ አድርጎ
ገልጾታል — ‹‹ከልብሰ የአምር እግዚሉ፤ ውሻ
ጌታውን ያውቃል››። ጌታችንም በቅዱስ ወንጌል
በውሻ የተመሰለችውን ከነናዊቷን ሴት ስለ

ታማኝነቷ አድንቋታል፤ ልጅዋንም ፈውሶላታል።
(ማቴ.፲፭÷፳፩-፳፰)
ማዕተብን ከሚቃወሙ አንዳንዶች ‹‹ጽዳት
ያጎድላል›› በማለት ያመካኛሉ። በርግጥ
የጠንቋይ ክታብ የቃልቻ ግሣንግሥ መሰብሰቢያ
ካደረጉት የሥጋ ንጽሕናን ብቻ ሳይኾን
የሚያጎድለው የነፍስንም ጽዳት የሚያጎድል መኾኑ
ዕውቅ ነው። ማተብ እና መስቀሉ ግን ጽዳት
ያጎደለበት ጊዜ ስለሌለ ሰበብ አያዋጣም።

ስለዚኽ የክርስትናችንን ዓርማ የነፍሳችንን ሰንደቅ ዓላማ በነፃነት ስናውለበልብ ለመኖር ያብቃን፡፡

አሜን፡፡

ምንጭ፡- መለከት መጽሔት፤ ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፮፤ ሚያዝያ ፲፱፻፹፯ ዓ.ም.

የቤተክርስትያን ከበሮ እና ድንቅ ምሳሌው

የከበሮ አመታት፦ ከበሮ ሲመታ ቀጥ ተብሎ አይመታም፤ መዘምራን ግራና ቀኝ እያሸበሸቡ ይመታሉ ይህም ጌታ ከሐና ቀያፋ

፤ ከቀያፋ ወደ ጲላጦስ ያደረገውን እንግልት ያስታውሰናል፡፡* ከበሮ መጀመሪያ በርጋታ ይመታና በፍጥነት ይዘዋወራል ይህም ጌታችንን አይሁድ እንደያዙት መጀመሪያ በቀስታ እየዘበቱ ይመቱት ነበር፤ በኋላ ግን ጲላጦስ ተመራምሮ ነፃ ሳያወጣው የሰንበት ቀንም ሳይገባብን ኑ እንደብድበው የማለታቸው ምሳሌ ነው፡፡ በማሕሌት ላይ ከበሮው መሬት ላይ ተቀምጦ ሲመታ ጌታችን መሬት ላይ ወድቆ መንገላታቱን እናስባለን፡፡የከበሮ 2 ክፍሎች፦ ከበሮ ስታስቀምጡ ሁልጊዜ ሰፊው አፍ ወደ ላይ መሆን አለበት፤ ትንሹን ክፍል ወደ ላይ ካስቀመጥን ግን

ስህተት ነው። ሰፊው የከበሮ ክፍል የመለኮት ምሳሌ ነው፤ ይህም የጌታችንን የባህርይ አምላክነትና ምሉዕ በኵለሄ መሆኑን ለሥላጣኑ ወሰን ድንበር እንደሌለው የሚያስታውሰን ነው። ጠባቡ የከበሮ ክፍል ደግሞ የትስብእት ምሳሌ ነው፤ ይህም ጌታችን በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት ተወስኖ ሥጋን ተዋህዶ መገለጡንና የዮሐንስ ወንጌልን ያስታውሰናል፦*በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ "ቃልም እግዚአብሔር ነበረ … ቃልም ሥጋ ሆነ" [ዮሐ. 1-14]ከበሮ የሚለብሰው ልብስ አይሁድ ጌታን ያለበሱት የቀይ

ከለሜዳ ምሳሌ ነው፡፡ በከበሮው ላይ የተጠላለፈው ጠፈር በጌታችን ጀርባ ላይ የታየው የግርፋት ሰንበር ምሳሌ ነው፡፡ የከበሮው ማንገቻ አይሁድ ጌታን የጎተቱበት ገመድ ምሳሌ ነው፡፡ቤተክርስቲያን ከጣራዋ እስከ መሬቷ ሁሉም ሥርዓቷ ያስተምራል ፤ ባህረ ጥበብ ቤተክርስቲያን እየተናገረች ታስተምራለች ሳትናገር ዝም ብላም ታስተምራለችና!! ወስብኃት ለእግዚአብሔር

.......ክርስቲያናዊ

አለባበስ.....ለመላው ክርስቲያኖች

መሰልጠን ወይስ መሰይጠን? (ሼር የተደረገ መልክት ነው)
"ሴትም ራስዋን ባትሸፍን ጠጉርዋን ደግሞ ትቆረጥ፤ ለሴት ግን ጠጉርዋን መቆረጥ
ወይም መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ ራስዋን ትሸፍን።
ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለ ሆነ ራሱን መከናነብ አይገባውም።"
1ኛ ቆሮ 11፥6-7
“ሴት የወንድን ልብስ አትልበስ ወንድም የሴትን ልብስ
አይልበስ ይህን የሚያደርግ በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ
የተጠላ ነው።” ዘዳ. 22፡5
ስለ አለባበሳችን እንወያያለን ዛሬም

እህቶቻችን ላይ
እናተኩራለን አበዛኸው ምነው እኛን
ብቻ እንደማትሉኝ ተስፋ
አደርጋለው፡፡
ስለ አለባበስ መነጋገር ያስፈለገን
እውነተኛ ክርስቲያን
በአነጋገሩ፣ በአረማመዱ፣
በአመጋገቡ፣ በአለባበሱ፣ ብቻ
በሁሉ ነገሩ የተለየ መሆን ስላለበት
ነው ይኸውም ሁሉን
በአግባብና በሥርዓት ስለማድረግ
ነው እህቶቻችን ላይ
ማተኮር ያስፈለገው ደግሞ
በአብዛኛው በዚህ ረገድ ትችት
የሚበዛው እነሱ ላይ ስለሆነ ነው፡፡
እነሆ ውድድሩ ከዕለት ወደ ዕለት
እየጨመረና እየከፋ ነው

ለመልካም ነገር መወዳደር ባልከፋ ነገር ግን በከተማችን
በተለይም በዋና ዋና መንገዶች ላይ የምናየው የእህቶቻችን
አለባበስ አንዷ ከሌላዋ ልቃና በልጣ ለመታየት የሚደረግ
ግብግብ እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡ በእርግጥ
እህቶቻችን በዚህ እንደማይስማሙ እናውቃለን አብዛኞቹም
ስለተመቸኝና የምወደው አይነት አለባበስ ስለሆነ ነው እንዲህ
የምለብሰው ይሉናል ይሁን እንጂ እውነታው ሌላ ይመስላል
ምክንያቱም:-
* ብርድልብስ ለብሰን እንኳን በማንቋቋመው የብርድ ወቅት

ሰውነትን በቅጡ የማይሸፍን ብጣሽ ጨርቅ ጣል አድርጎ
መውጣት እንዴት ያለ ምኞት ነው?
*እጅግ አስጨናቂ ሙቀት ባለበት ሰዓት ሰውነት ላይ ተጣብቆ
ሌላ ጭንቀት የሚፈጥር አለባበስ እንደምን ብሎ ያስደስታል?
ዓላማችን ምንም ይሁን እሱ ላይ የመከራከር ፍላጎት የለንም
ነገር ግን አለባበሳችንን እንደ ክርስቲያን እንፈትሸው ዘንድ
ይገባልና ይህ ተፃፈ
መሰልጠን ወይስ መሰይጠን?
አብዛኞቹ ሴቶች ይህን ተግባር ስልጣኔ እንጂ ስህተት ነው
ብለው አያምኑም፡፡ ለነዚህ ሴቶች

ከኃይማኖት ብቻ ሳይሆን ከባህላችን ጭምር ያፈነገጠውን የምዕራባውያን አለባበስ መልበስ ዘመናዊነት ነው። ላንቺስ? መጽሐፍ ቅዱስስ ምን ይላል?

--------------------------------

-----------//////////////////////

ማንኛዋም ሴት የሰውነቷን ቅርፅ የሚያሳይ ወይም ክፍትፍት ልብስ ለብሳ መሄዷ የሁሉንም ወንዶች ስሜት መፈታተኗ እርግጥ ከመሆኑም በላይ በመንፈሳዊ ህይወት ደካማ የሆኑትን ደግሞ ለኃጢያት አጋልጦ ይሰጣል። እዚህ ላይ የተሳሳተው በራሱ ደካማነት ነው

ብሎ ምክንያት መስጠት
አይቻልም እግዚአብሔር
የሚጠይቀው በማን ተሰናከለ
የሚለውን ጭምር ነውና በክርስትና
ደግሞ ሰውን ማሰናከል
እጅግ የከፋ ኃጢያት ነው፡-
“ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን
የሚያሰናክል የወፍጮ ድንጋይ
በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባህር
መስጠም ይሻለው ነበር፡፡”
ማቴ. 18፡6
አንዳንድ ሴቶች እግዚአብሔር ምን
ሰራሽ እንጂ ምን ለበስሽ
አይለኝም ይላሉ እግዚአብሔር ግን
እንዲህ ይላል
“እንግዳ ልብስ የሚለብሱትንም
ሁሉ እቀጣለው፡፡” ትን.ሶፎ.

1፡18
እንግዲህ የሴቶቹን እንቀበል ወይስ የእግዚአብሔርን
ምርጫው ያንቺው ነው እህቴ መጽሐፍ ግን እንዲህ ይላል፡-
“ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል።” የሐዋ. 5፡
29
በሴቶችና በወንዶች መካከል የአለባበስ ልዩነት ሊኖር ይገባል
“ሴት የወንድን ልብስ አትልበስ ወንድም የሴትን ልብስ
አይልበስ ይህን የሚያደርግ በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ
የተጠላ ነው።” ዘዳ. 22፡5 ታዲያ ቀሚስን የወንድ ሱሪን የሴት ማን
አደረገው? ይህ

የሰነፍና ለስህተታቸው ምክንያትን የሚሹ ሴቶች የሚያነሱት ጥያቄ ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል አውቀን ልንፈፅመው እንጂ በቃሉ ላይ የምንፍቅና ጥያቄ እናነሳ ዘንድ ተገቢ አይደለም ግን ደግሞ ተፈጥሯችንን ብቻ በማየት ህሊናችን እራሱ ቢናገር ሱሪ የሴት ነውን? ቀሚስስ የወንድ ነው እንዴ "ተፈጥሮ እንኳን አያስተምራችሁምን? 1ኛ ቆሮ. 11፡14

"ዳሩ ግን ማንም ሊከራከር ቢፈቅድ እኛ ወይም የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ያለ ልማድ

የለንም።” 1ኛ. ቆሮ. 11፡16
ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ስህተት
መሆኑን መናገር እንጂ
መከራከር አያስፈልግም ክርስትና
በምርጫ ነውና።
እዚህ ላይ ግን ቀሚስ ሲባል
ከውስጥ ሱሪ የማይሻለውን
ብጣሽ ጨርቅ እንዲሁም ቁመቱ
ረዥምም ሆኖ ከሰውነት ጋር
የሚጣበቀውን አይነት አለባበስ
ማለት እንዳልሆነ ልብ
እንበል።
እህቶቻችን ሆይ ማስተዋልን
ትላበሱ ዘንድ እንለምናችኋለን
መሰልጠንና መሰይጠንም ትለዩ
ዘንድ ይሁን ሰውነትሽ
የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነውና

ሁሉን በአግባብና በሥርዓት
አድርጊለት፡፡
ደግሞም ክርስትና ራስ ወዳድነትን
አብዝታ ትጠላለች ምንም
ነገር ስናደርግ ስለ ሌላው ሰው
ልናስብ ያስፈልገናል እኛስ
ሰውን ወደ ዝሙት ሊያመራው
ስለሚችል አለባበሳችን እጅግ
ተጨነቅን ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ
ወንድማችንን
ስለማሰናከል ምን አለ
“መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው
ከሆነ ወንድሜን
እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ
አልበላም፡፡” 1ኛ.ቆሮ 8፡
13
እንግዲህ ክርስትና እዚህ ድረስ ነው

ስለራሳችን ብቻ ሳይሆን
ስለ ወንድሞችና እህቶቻችን
የምናስብባት ለእነሱም መሰናከያ
እንዳንሆን እየተጠነቀቅን ሁሉን
በአግባብና በሥርዓት
የምናደርግባት፤ እምነታችንን
በምግባር የምንገልጽባት ናት።
“በእውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን
ነብር ዝንጉርጉርነቱን ይለውጥ
ዘንድ ይችላልን። ትን.ኤር. 13፡27
እህቴ ሆይ አንቺም ኤርሚያስ
እንዳለው ኢትዮጵያዊነትሽን
ጠብቂ የምዕራባውያን በዓል
ከሆነው አለባበስም ሆነ
የምንዝር ጌጥ ራስሽን አርቀሽ
በሚያኮራው ኢትየጵያዊ
ባህላችን ትዋቢ ዘንድ እግዚአብሔር

ይርዳሽ፡፡
ለሁላችንም አስተዋይ ልቦና ይስጠን፡፡ አሜን!!!!
ሁላችን ምግባር ያለው እምነት እንዲኖረን እግዚአብሔር ይርዳን፡፡ አሜን!!!

መቁዋሚያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን !
መቁዋሚያ ምሳሌነቱ ፦ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሸከመውና የተሰቀለበት ቅዱስ መስቀል ምሳሌ ነው ፡፡
በሥርዓተ ማህሌት ጊዜ መዘምራኑ

መጀመሪያ መቁዋሚያቸውን ከላይ ወደ ታች ያደርጉታል ::
ይህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት መውረዱን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሱዋ ነፍስ ነስቶ መወለዱን ያመለክታል ከዚያም ዓለምን ዞሮ ማስተማሩን ለማጠየቅ መቁዋሚያውን ከግራ ወደ ቀኝ ያሽከረክሩታል ::
መዘምራኑ መቁዋሚያቸውን ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ የሚያደርጉት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐና ቀያፋ ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ መመላለሱን መከራ መቀበሉን ለማሳሰብ ነው ::

መቁዋሚያውን ወደ መሬት የሚደስቁት የማይሞት ጌታ ወደ መቃብር ወረደ ሲሉ ነው ። ወደ መሬት የደሰቁትን መልሰው ወደ ላይ ማንሳታቸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ መነሳቱን ለመመስከር ነው ።

በተመሳሳይ ሁኔታ ከቀድሞ በበለጠ ከፍ አድርገው በኃላ ረጋ ብለው የሚመልሱት ዕርገቱንና ዳግም ምፅዓቱን ለማዘከር ነው ። ሞቶ የተነሳው ተነስቶም ያረገው ዳግመኛ ይመጣል ሲሉ ነው ።

የአብ ጸጋ የወልድ ቸርነት የመንፈስ ቅዱስ አንድነት የእመቤታችን አማላጅነት የቅዱሳን

መላእክት ፈጣን ተራዳዒነት ጥበቃቸው የፃድቃን ሰማዕታት የቅዱሳን ሐዋሪያት የአበው መነኮሳት ምልጃ ጸሎት ቃል ኪዳናቸው ረድኤት በረከታቸው ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን አሜን አሜን !!!

ለምን ነጭ ነጠላ እንለብሳለን?

አንዳንዶች ባለማወቅም ይሁን በቅናት ክርስትና ነጠላ ለብሶ ቤተክርስቲያን መሄድ አይደለም ሲሉ ይደመጣሉ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ግን መጽሐፍ ቅዱስን ምክንያት አርጋ ምሥጢሩን ከተግባር ጋር

ትገልጻለች ወደ ቤተ መቅደስ ስንሄድ ነጭ መልበሳችን የተገባ ነው ነጭ ነጠላ ጋቢ አደግድገን ወይም በትእምርተ መስቀል ለብሰን ቤተመቅደስ ስንቆም የምናስባቸው ምስጢራት አሉ

ለምን በትእምርተ መስቀል እንለብሳለን ካልን የክርስቶስን መከራ ለማሰብ ነጠላው ወደ ግራ ቀኝ በትእምርተ መስቀል አምሳል ይጣፋል። በዚህ ጊዜ ጌታችን በዕለተ አርብ የተቀበላቸው ጸዋትወ መከራ እንዲሁም በቀራንዮ በምልዕልተ መስቀል መሰቀሉን ያስታውሰናል።ይኸውም የተመሳቀለ ነጠላ የሚመለከትም ሁሉ የጌታችንን መከራ መስቀል

መቀበሉን ያስባል። የምናጣፋው ነጠላ ነጭ የሆነባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ እነዚህ ከታች የተጠቀሱት ምክንያቶች ሰፊ ትምህርት ቢኖራቸውም እኔ ግን ባጭሩ እንዲህ አቀረብኩላችሁ፦

፩. የሚጠብቀንን ሰማያዊ ክብር በማሰብ ነጭ እንለብሳለን ".....ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ እስከመቼ አትፈርድም? ደማችንንስ በምድር ላይ በሚኖሩት ላይ እስከመቼ ድረስ አትበቀልም አሉ ለእያንዳንዳቸው ነጭ ልብስ ተሰጣቸው....." /ራዕ.፮÷፱-፲፩/ "ከዚህም በኋላ አየሁ እንሆም አንድ እንኳን ሊቆጥራቸው የማይችል ከህዝብና ከነገድ

ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባም የዝንጣፊም በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ" /ራዕ.፯፥፱/

፪.ቅዱሳን መላእክት ከእኛ ጋር መሆናቸውን ማሰብ".....ማርያም ግን እያለቀሰች ከመቃብር በስተ ውጪቆማ ነበር፡፡ ስታለቅስም ወደ መቃብር ዝቅ ብላ ተመለከተች ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው የጌታ የኢየሱስ ሥጋ በነበረበት ቦታ አንዱ በራስጌ ሌላው በግርጌ ተቀምጠው አየች፡፡" /ዮሐ.፳፥፲፩-፲፪/ ታድያ እንደ መላእክት ለብሶ በቤተክርስቲያን ማገልገል ምኑ ነው የሚያስወቅሰው

ያሚያሳፍረው ያኮራል እንጂ!።
፫. ከጌታችን ጋር እንዳለን እናስባለን
".....ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ለብቻቸው አወጣቸው። በፊታቸውም መልኩ ተለወጠ ፊቱም እንደ ፀሐይ አበራ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ሆነ።" /ማቴ.፲፯፥፩-፪/ስለዚህም ነጠላ መልበስ መንፈሳዊ ትርጉም አለውና ወንዶች ብንሆን በኪዳኑ በቅዳሴውና በንግሱ ላይ ያለ ነጠላ ከምንሄድ ነጠላ ብንለብስ እህቶቼም ሥርዓቱን የጠበቀ ነጠላ ለብሰን ከላይ የተጠቀሱትን እያሰብን በቤቱ

ብንገኝ መልካም ነው፡፡ << አባቶች የሠሩትን የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ>> /ምሳሌ.፳፪፥፳፰/ ሁላችንም ሥርዓተ ቤተክርስትያንን እንድንጠብቅ ልቦና ይስጠን፡፡ እግዚአብሔር ሁላችንንም እንደ ፍላጎታችን ሰይሆን እንደ እርሱ ፈቃድ እንድንመራ ዓይነ ልቦናችንን ያብራልን! ይህ እራስን መግዛት ለቃሉ አለመታዘዝ ብዙዎቻችን ጋር ያለ ችግር ነው ይህ የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጣችን ሳይኖር የዓለምን ፍቅር እብልጠን ምን ችግር አለው እያልን በእግር ብቻ በቤቱ መመላለስ ስለለምድን ነው፡፡ ትልቁ ችግር ያመጣው ምን ችግር አለው ነው

ለዚህም ማሳያ የፕሮቴስታንት እምነት ያለ ዶግማና ቀኖና በራሳችን አስተያየት የምንጓዝ ቢሆን ብዙ ድርጅት በሆንን ነበር ግን አንድ ሀሳብ አንድ አላማ የሚያረገንን ዶግማና ቀኖና ቤተክርስቲያናችን ሰርታልናለች ስለዚህም ትክክል ያልሆነውን የዓለም ስርአት ስለተለማመድነው እንደ ቤተክርስቲያን ስርዓት ለመመላለስ ይቸግረናል ከመምህረ ንሰሃችን ጋር በመመካከር፤ በግልና በማህበራዊ ጸሎቶች በመትጋት፤ አንዱ ለሌላው 43 43 በመጸለይ፤ ሁል ግዜ ቅዱሳት መጽሐፍትን በማንበብና ሊያዘናጉን ከሚችሉ ሁኔታዎች በመራቅ

ለእግዚአብሔር ሕግ መገዛት እንችላለን ትእዛዙን ፈጽመን ለመኖር የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ሁላችንንም ይርዳን!!!

## ጽንሃ ~

ጽንሃ የእጣን ማሳረጊያ ወይም ማጠኛ ነው :: ሦስት ሰንሰለቶች አሉት በሰንሰለቶቹ ላይ ቢያንስ አስራ ሁለት (12) ቢበዛም ሃያ አራት (24) ሻኩራዎች ይኖሩታል :: ከስሩ እጣኑ የሚቀመጥበት ሙዳይ የመሰለ ክፍል አለው ::

ይህም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ሲሆን ÷ መለኮት ከሥጋዋ ሥጋ ነፍሱዋ ነፍስ ነስቶ ሰው መሆኑን ያመለክታል ።

ፍህሙ የጌታችን የመለኮትነቱ ምሳሌ ሲሆን እጣኑ እንደሚቃጠልና መዓዛው ሁሉን እንደሚያውድ ምዑዘ ባሕርይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ብዙዎች ኃጢያት ራሱን መስዋዕት በማድረግ አቅርቦ ዓለሙን ሁሉ ማዳኑን ያጠይቃል ።

3 ሰንሰለቶቹ ሶስት መሆናቸው የሚስጢረ ሥላሴ ምሳሌ ነው ።

የሻኩራዎቹ ቁጥር አስራ ሁለት (12) መሆኑ የሐዋሪያት ምሳሌ ነው ።

ሃያ አራት (24) መሆኑ ደግሞ የሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ምሳሌዎች ናቸው ።

የመንፈስ ቅዱስ በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን አሜን አሜን !!

Miko ZE Ethiopia

# ጸናጽል

ከብርና ከነሐስ ከሌላም ብረት የሚሰራ ነው።

እንዲሹአሹአ የብረት ቅጠል

ይደረግበታል
አገልግሎቱም ለእግዚአብሔር ክብር ይዘመርበታል:
ጸናጽል ከከበሮ ጋር አብሮ የሚሄድ የዜማ ዕቃ ነው::
# ምስጢሩ
በግራና ቀኝ ያለው ዓምድ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ምሳሌ ነው::
-በሁለቱ ዓምዶች መሐል ያሉት ሁለቱ ቀጫጭን ዘንጎች ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ መላዕክት ሲወጡባት ሲወርዱባት ያያት መሰላል ምሳሌ ነው::
-በዘንጎቹ ላይ ያሉት የብረት ቅጠሎች ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ በመሰላል ላይ ሲወጡ ሲወርዱ ያያቸው መላእክት ምሳሌ ነው::

በሌላ በኩል የብረት ቅጠሎቹ ብዛት ቢያንስ አምስት ቢበዛ ሰባት ይሆናል::

አምስት ሲሆን የአምስቱ አዕማደ ምስጢር ሰባት ቢሆን ደግሞ በሰባቱ ሰማያት ይመሰላል::

-የብረት ቅጠሎቹ በመጀመሪያ ዘንግ ላይ ሁለት ይሆናሉ:

ይህም ወልድ ሁለት ልደት ቅድመዓለም ያለ እናት ኃላም አዳምን ለማዳን ያለ አባት ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱ

-በሁለተኛ ዘንግ ላይ ሶስት ሲሆኑ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል::

-ድምጹ ያማረና መልካም መሆኑ በመላዕክት ዜማ ይመሰላል::

-ወዲያና ወዲህ መባሉ የጌታችን በአይሁድ መንገላታት ምሳሌ ነው::

"የምናስተውል ካለን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል"፤

※ በሚሞት ስጋችሁ ሐጢያት አይንገስ
ብልቶቻችሁን የፅድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ (ሮሜ 6፥12-14)

※ ከሴት ጋር አለመገናኘት መልካም ነው ካልተቻለ ዝሙትን ለመከላከል በአንድ ይፅና ከዚህ ውጭ ጉዞ ወደ እሳት ነው (1ኛ ቆሮ 7፥1)

※ ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱ ያፈርሰዋል ቤተ መቅደሱም እናንተው ናችሁ (1ኛ ቆሮ 3÷17)

※ ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእረፍትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸፍኑ (1 ኛ ጢሞ 2÷9)

※ የወንድ ልብስ የለበሰች ሴት በአምላክ ዘንድ የተጠላች ናት (ዘዳ 22÷5; ዘፀ 39÷28)

※ ፀጉሯን ሳትሸፍን የምትፀልይ ሴት እራሷን ያዋረደች ናት(1ኛ ቆሮ 11÷5)

※ የወይን ጠጅ ከሚጠጣ ጋር አትቀመጥ (ምሳ 23÷20)

※ ዘፈን የሰነፎች ዜማ ነው (መክ

7፥5)

※ በዛም አጋንንት ይዘፍናሉ (ኢሳ 13፥21)

ቤርዜሊ ተስፋዬ

ጸ ናጽል

የጸናጽልን ትርጎም ለጠየቃችሁኝ በሙሉ

በ ዲ/ን ቤርዜሊ ተስፍዬ

ጸናጽል ማለት በቁሙ ሻኩራ ቃጭል ማለት ነው።ጸናጽል አበው እግዚአብሔርን ያመስገኑበት የተቀደሰ ንዋይ ፡የመዝሙር መሳሪያ ነው

፩ኛ ዜና ፲፫፥፰ ዳዊት እና

እስራኤል ሁሉ በቅኔና በበገና፤በመሰንቆ ና በከበሮ በጸናጽል እና በመለከት በእግዚአብሐሬ ፊት በሙሉ ሐይላቸው ይዘምሩ ነበር።

መዝ፻፶፥፭ ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት

፩ኛ ቆሮ ፲፫፥1በሰዎች እና በመላዕክት ልሳን ብናገር ፍቅርግን ከሌለኝ እንደ ሚጮኽ ነሐስ ወይም እንደሚንሸዋሸው ጸናጽል ሆኜለው

የጸናጽል አሰራር እና ምሳሌአዊ ትርጉም

ጸናጽል የ "ሀ" ቅርፅ አይነት ያለው ሲሆን የሚሰራውም ከብር፣ከነሐስ ፣ከወርቅ ይሰራል በ"ሀ"ቅርጽ መሀል ለመሀል ሁለት ዘንጎች እንዲኖሩት ይደረጋል በዘንጎቹላይ

ቅጠሎች \ሻኩራዎች/ ይንጠለጠላሉ እነዚህ ሻኩራዎች ቁጥራቸው የታወቀና የተወሰነ ነው ከላይ ቀስት የሚመስል ደጋን ይሰራል

"ሀ" ቅርፅ ያለው ከታች ለመገዣ እንዲሆን እጀታ ይሰራለታል

በግራና በቀኝ ያሉት ሁለቱ አምዶች

የሁለቱ ኪዳናት የብሉይ እና የሀዲስ ኪዳን ምሳሌዎች ናቸው

ጸናጽሉን የሚያፀኑት እና የሚያቆሙት ሁለቱ አምዶች እድሆኑ ሁሉ ሃይማኖትም የሚፀናው በብሉይ እና በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ነው ::

ሁለቱ ጋድሞች

በሁለቱ አምዶች መካከል

የሚዘረጉ ሻኩራዎችን የሚይዙ ሁለት ጋድሞች አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ተኝቶ መላዕክት ሲወጡባት ሲውርርዱባት ያያት የብረሀን መሰላል ምሳሌ ነው ፡፡ዘፍ ፳፰÷፲፪

እነዚህ ጋድሞች /የተጋደሙት / ሁለት የሆኑበት ምሳሌ

1የክርስቶስን ሁለት ልደታት ምሳሌዎች ናቸው

እነርሱም ቅድም ዓለም ከአብ ያለእናት መወለዱን

ድህረ አለም ከድንግል ማርያም ያለ አባት መወለዱን ሲገልፁ ነው

2 የፍቅረ ቢጽ ና የፍቅረ እግዚአብሔር ምሳሌ ናቸው መላዕክት ጋድሞቹን እየረገጡ

ወደላይ ሲወጡ ወደታችም ሲወርዱ እንደነበር አባታችን ያዕቆብ አይቱል

ሰውም ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍውረ ቢጽን ገንዘብ አድርጎ ወደ መንግስተ ስርማያት እንዲገባ ለማጠየቅ ጋድሞቹ ሁለት ሆነዋል ::

3የደቂቀ አዳም እና የደቂቀ መላዕክት ምሳሌ ናቸው

በጋድሞቹላይ እየወጡና እየወረዱ የታዩ ቅዱሳን መላዕክት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይዘምሩ ነበር በሐዲስ ኪዳን ከቅዱሳን መላዕክት ጋር ደቂቀ አዳምም በአንድነት ሆነው እንዳመሰገኑ ለማጠየቅ ነው ::ሌላው ሁለቱን

ጋድሞች ስናይ ደቂቀ አዳም ከቅዱሳን መላዕክት ጋር እንዳመሰገኑ እናስባለን ::

ቅጠሎቹ ወይም ሻኩራዎቹ የቅዱሳን መላዕክት ምሳሌዎች ናቸው ስናወዛውዘው ድምፅ መስጠቱ ያዕቆብ ያያት መሰላል ላይ ሲወጡ ሲወርዱ ያመሰገኑት የመላዕክት ምስጋና ድምፅ ምሳሌ ነው::

የሻኩራዎቹ ቁጥር በጋድሞቹ ላይ የተለያየ መጠን\ቁጥር/ ያላቸው ሻኩራዎች ሊደረጉ ይችላሉ

አምስት ከሆኑ የአምስቱ አዕማደ ምስጢር ምሳሌ

ስድስት ከሆኑ የስድስቱ ቃላተ

ወንጌል ምሳሌ

ሰባት ከሆኑ የሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ምሳሌ ይሆናል ማለት ነው ።

ጸናጽል በቀስተ ደመና መሐርብ

በጸናጽል ላይ የምናገኘው ቀስተደመና መያዣ ለኖህ የተሰጠው ቃልኪዳን ምሳሌ ነው ።እግዚአብሔርም አለ በእኔና በአንተ መካከል ካንተም ጋር ባለው በህያው ነፍስ ሁሉ መካከል ለዘለአለም የማደርገው የቃል ኪዳን ምልክት እሄነው ቀስቴን በደመና አድርጌለው የቃል ኪዳኑም ምልክት በእኔና በምድር መካከል ይሆናል ዘፍ ፱፥፲፪ ፥፲፫

# የኖህ ቀስተ ደመና ትርጉም

በጥንት ዘመን ቀስት የያዘ ሰው የቀስቱን ደጋን ወደራሱ አዙሮ ከተገለጠ ለጠብ ሳይሆን ለሰላም እንደመጣ ይታወቅ ነበር ። ደጋኑን ወደሰዎች አዙሮ ከተገለጠ ግን ለጠብ እንደመጣ ይታወቃል ለኖህ የተገለጠለት ቀስተደመና ደጋኑ ወደምድር የዞረ ቢሆን እግዚአብሔር እንደተጣላን ያመለክት ነበር ። ነገር ግን የዚህ ቀስት ደጋን ወደ ሰማይ ወደ እግዚአብሔር የዞረ ስለሆነ እግዚአብሔር በአይነ መአት ሳይሆን በሰላም እንደጎበኘን ያመለክታል ስለዚህ የኖህ ቃል ኪዳን የምህረት ምልክት ነው።

አባቶቻችን የቀስተ ደመና በላዩ በተሰራበት ጳናጽል ሲያመሰግኑ ኪዳነ ኖህን አስበህ እርዳን ምስረን ይቅር በለን ማለታቸው ነው ።
እቺን ምስጢር የገለፀልን አምላክ ስሙ የተመሰገነ ይሁን

ስንዴ ና # ወይን ለምን ለጌታችን ስጋና ደም ተመረጠ???
# ሼር እናርግ ማንበብም እዳንረሳ
ስንዴና ወይን የተመረጠበት ምክንያት ዘፍ 14÷18 የሳሌም ንጉስ መልከ ጼዴቅም እንጀራና የወይን ጠጅን አወጣ እርሱም የልኡል እግዚአብሔር ካህን ነበር

ይላል

ካህኑ መልከ ዔዲቅም በስንዴና በወይን መስዋቱን ይሰዋ እንደነበረ በመፅሀፍ ተፅፎ ስለሚገኝ እንዲሁም በአዲስ ኪዳንም ደግሞ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ እብራዊያን 7÷1-3 የሳሌም ንጉስ የልኡል እግዚአብሔር ካህን የሆነ ይህ መልከ ዔዲቅ አብርሀም ነገስታትን ድል ነስቶ በተመለሰ ጊዜ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው አብርሃምም ከገንዘቡ ሁሉ ከ 10 አንድ ሰጠው መጀመሪያ የስሙ ትርጓሜ የፅድቅ ንጉስ ነበር በኋላ የሳሌም ንጉስ ተባለ የሰላም ንጉስ ማለት ነው

አባት የለውም እናት የለችውም

ትውልዱም አይታወቅም ለዘመኑም መጀመሪያ ለህይወቱም መጨረሻ የለውም

ክህነቱ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ ለዘለአለም ይኖራል

የመልከ ጼዴቅ ክህነትና መስዋት የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ ለዘለአለም ስለሚኖር የወልደ እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ እንደሚያገለግል ስለሚያመለክት ነው አንድም

በ መዝ 4÷7 በልባችን ደስታን ጨመርህ ከስንዴ ፍሬና ከወይን ከዘይትም ይልቅ በዛ ብሎ ስለወይንና ስለስዴ መመረጥ በትንቢት ይናገር ነበረ

ስለዚህ እነዚህን ምሳሌ አድርጋ ቤ/

ክርስቲያን ወይን የጌታችን የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትኩስ ደም ስንዴ ደግሜ የጌታችን የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ መስላ ትጠቀምበታለች

ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና በምድር ላይ ሲኖሩ ምግባቸው ስንዴና ወይን እንደነበረ በእውነተኛ ሕይወታቸው ጌታም ይህንን ምግብ ይህንን ዘር መርጦ ስለነበረ ነው

ሚስጥሩ ደግሞ ስንዴ ስብ ስጋን ስለሚመስል ወይን ደግሞ ትኩስ ደም ስለሚመስል ነው

ስለዚህ እነዚህን ምሳሌ አድርጎ

የተሰጠ ነው ማለት ነው

ኦርቶዶክስ መልስ አላት/Orthodox Have An Answer

ድርሳንና ገድላት ጥያቄ ✒

ጥያቄ -->በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ጊዜ ድርሳንና ገድል ሲባል እሰማለሁ፡፡ እኔም የድርሳንና የገድል ልዩነት ብዙ ጊዜ አይገባኝም፤ እባካችሁ የድርሳንና የገድልን አንድነትና ልዩነት አስረዱኝ”

-ገብረ እግዚአብሔር

ከዲላ

በዲ/ን ኀሩይ ባየ

ውድ ጠያቂያችን በእርግጥ እርስዎ

እንዳሉት ድርሳንና ገድል በቤተ ክርስቲያን የማይነሡበት ጊዜ የለም፡፡ “የኑሮአቸውን ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነት ምሰሏቸው” (ዕብ.13÷7) እንደተባለው በሃይማኖትና በምግባር ለመጠንከር ገድለ ቅዱሳንን የያዙ መጻሕፍትን እናነባለን፤ እንጸልይባቸዋለን፡፡ የቅዱሳን መላእክትንም ጠባቂነት፣ የሊቃውንትን ተግሣጽ ትርጓሜና ምክር የዕለተ ሰንበትን ክብር እና የኢየሱስ ክርስቶስን የቤዛነት ሥራ የሚናገሩ ድርሳናትን ሁል ጊዜ እናነባለን እናደርሳለን፡፡

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት

ሐዲስ በተባለው መጽሐፋቸው “ድርሳን” የሚለውን ቃል እንዲህ ብለው ይፈቱታል “ድርሳን በቁሙ “የተደረሰ፣ የተጣፈ፣ ቃለ ነገር፣ ሰፊ ንባብ፣ ረዥምም ስብከት፣ ትርጓሜ፣ አፈታት፣ ጉሥዐተ ልብ፣ መዝሙር፣ ምሥጢሩ የሚያጠግብ፣ ቃሉ የተሳካ፣ ጣዕመ ቃሉና ኃይለ ቃሉ ደስ የሚያሰኝ ልብ የሚነካ” ማለት ነው።

ድርሳን ስለ ቅዱሳን መላእክት፣ ተራዳኢነት ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ክብርና ጸጋ፣ ስለ ዕለተ ሰንበት ክብርና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ የሚናገሩ /የሚያትቱ/ መጻሕፍት ማለታችን

ነው።
እስከ 2000 ዓ.ም በተደረገው ጥናት ወደ 138 የሚሆኑ በድርሳን ስያሜ የሚጠሩ መጻሕፍት እንዳሉ ታውቋል። ከእነዚህም ውስጥ 11ዱ የመላእክት ድርሳናት ሲሆኑ የ11ዱ መላእክት ስምም ቅዱስ ሚካኤል፣ ቅዱስ ገብርኤል፣ ቅዱስ ሩፋኤል፣ ቅዱስ ራጉኤል፣ ቅዱስ ዑራኤል፣ ቅዱስ አፍኒን፣ ቅዱስ ፋኑኤል፣ ቅዱስ ሳቁኤል፣ ቅዱስ ሱርያል፣ ቅዱስ ሱራፌልና ቅዱስ ኪሩቤል ናቸው።
የመላእክትድርሳናት በአብዛኛው ተመሳሳይነት ባሕርይ አላቸው። የውስጥ ይዞታቸውም በ5 ይከፈላል። እነሱም መቅድም፣

ድርሳን፣ ተአምራት፣ አርኬና መልክእ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ድርሳን የምንለው የባለ ድርሳኑን መልአክ ግብር በፈጣሪው ዘንድ ያለውን ሞገስ የሠራቸውን ተአምራት ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እያጣቀሰ የሚያብራራ ክፍል ነው፡፡ በአጠቃላይ ድርሳንን በ4 መክፈል ይቻላል፡፡

ድርሳነ መላእክት የሚባለው ድርሳነ ሚካኤል ድርሳነ ገብርኤልን የመሳሰሉትን ነው፡፡

ድርሳነ ሰንበት ስለ ዕለተ ሰንበት ክብር የሚያብራራ መጽሐፍ ድርሳነ መስቀል ደግሞ የመስቀሉን ታሪክና አመጣጥ ይተርካል፡፡

ድርሳነ ሊቃውንት ደግሞ የእነ ቅዱስ አትናቴዎስ የእነ ቅዱስ ኤፍሬም ድርሳን የሚባለው ነው። ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ድርሳን ዘቅዱስ ቄርሎስንም ያጠቃልላል።

ድርሳነ ማኅየዊና ድርሳነ መድኅኔ ዓለም የመሳሰሉት ድርሳናት የኢየሱስ ክርስቶስን ጸዋትወ መከራ የሚያዘክሩ ድርሳናት ናቸው።

ገድል፡- "በቁሙ ትግል ፈተና ውጊያ ሰልፍ ድልና አክሊል እስ ኪገኝ ድረስ የሚደክሙት ድካም የሚሠሩት ሥራ የሚቀበሉት መከራ ማለት ነው" ሲሉ ደስታ ተክለ ወልድ በመዝገበ ቃላት ፍቺያቸው አስቀምጠውታል። አለቃ

ኪዳነ ወልድ ክፍሌም ገድል ማለት ጻድቃንና ሰማዕታት በሕይወት ዘመናቸው እያሉ የሠሩትን ሥራ የሚናገር መጽሐፍ እንደሆነ አብራርተዋል /ደስታ ተክለ ወልድ 2036፣ አለቃ ኪዳለ ወልድ ክፍሌ 301/ የገድል መጻሕፍት ጻድቃን፣ ሰማዕታት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ትእዛዘ እግዚአብሔር እንዲከበር ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን እንዲጠበቅ ከአላውያን ነገሥታት፣ ከቢጽ ሐሳውያን፣ ከጠላት ዲያብሎስና ከፈቃደ ሥጋ ጋር ያደረጉትን ተጋድሎ የሚያወሱ መጻሕፍት ናቸው፡፡ ሃይማኖታቸው በኑሮአቸው እንዴት እንደተገለጠ የሚያሳዩን የሕይወታቸው

መስተዋቶች ናቸው። ስለዚህ ገድል ስንል የቅዱሳን ታሪክ፣ ተአምራት፣ ቃል ኪዳንና መልእክት የያዘ መጽሐፍ ነው።ይህ እንዲህ ይሆናል ይቻላል ተብሎ የተነገረው ቃል በእውነት የሚኖር በቃልና በሥራም የሚገለጥ እንደሆነ የምናየው በቅዱሳን ገድል ነው። /ማቴ.10÷37፣ ሉቃ.14÷27፣ 1ቆሮ.11÷26-28/

ገድል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው /2ቆሮ.11÷23-22 ዕብ.11÷32-40/ ራሱ የሐዋርያት ሥራ የምንለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሐዋርያትን ግብር /ሥራ/ ገድልና ዜና የሚያስረዳ መጽሐፍ ነው። ከብሉይ ኪዳንም መጽሐፈ

ጦቢት መጽሐፈ አስቴር፣ መጽሐፈ ሶስና፣ የመሳሰሉት በሰዎቹ ኑሮ የተገለጠውን የእምነታቸውን ፍሬ የሚያሳዩ የገድል መጻሕፍት ናቸው።

ገድላት በ3 ይከፍላሉ እነሱም፡-

☞ ገድለ ሰማዕታት፡- ለምሳሌ ገድለ ጊዮርጊስ፣ ገድለ ፋሲለደስ፣ ገድለ ኢየሉጣ

☞ ገድለ ሐዋርያት፡- በአንድነት የተሰበሰቡ የሐዋርያት አገልግሎት ተአምራት መከራ የያዙ መጽሐፍት

☞ ገድለ ጻድቃን፡- ገድለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስና የመሳሰሉትን ነው።

ውድ ጠያቂያችን ምላሹን

ስለማጠቃለል ድርሳን ሲባል የመላእክትን ግብር በፈጣሪያቸው ዘንድ ያላቸውን ሞገስና የሠራቸውን ገቢረ ተአምራት እየዘረዘሩ የሚናገሩ፣ ስለ ዕለተ ሰንበትና ቅዱስ መስቀል ክብር የሚያስረዱ ድርሳነ ሰንበትንና የድርሳነ መስቀል፣ የመጻሕፍት ትርጓሜ ምክርና ተግሣጽ እንዲሁም ርትዕት የሆነችውን ሃይማኖት የመሰከሩበት የሊቃውንት መጻሕፍት፣ በመጨረሻም የኢየሱስ ክርስቶስን ጸዋትወ መከራ የሚያስታውሱ እንደእነ ድርሳነ ማኅየዊ ያሉት መጻሕፍት በድርሳን ሥር ይጠቃለላሉ፡፡

ገድል ደግሞ ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ጥበብ የቅዱሳንን መከራ ተጋድሎ፣ ተአምራትና ቃል ኪዳን የያዙ የቤተ ክርስቲያን ሕያውነት የሚገለጥባቸው መጻሕፍትናቸው፡፡ ድርሳናትም ሆኑ ገድላት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይጋጩ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያብራሩ የሚተረጉሙና የሚተነትኑ መጻሕፍት ናቸው፡፡ ሰፋ የለ ግንዛቤ እንዲያገኙ ሐመረ ተዋሕዶ 1999፥61፣ ሐመር ጥር/የካቲት 2000፥27 አዋልድ መጻሕፍት ማኅበረ ቅዱሳን፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት 1995፣ የኢዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትናንት

ዛሬና ነገ፣ ብራና ማተሚያ ቤት፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 1995፥16 የሚሉ መጻሕፍትና መጽሔቶችን ቢያነቧቸው መልካም ነው፡፡ እግዚአብሔር አምላክ በመላእክት ተራዳኢነት በቅዱሳን ጸሎት ሁላችንንም ይጠብቀን፡፡

Miko ZE Ethiopia

+++ ጥላ፦ በቅዳሴ ላይ ወንጌል ሲነበብ ጥላ ይዘረጋል ፤ ፀሐይ የለም ዝናብ የለም ለምንድን ነው ቢሉ ምሳሌው እንዲህ ነው፦ ክቡር ዳዊት "አቤቱ በክንፎችህ ጥላ ከልለኝ" ያለው ምሳሌ ነው ፤

አንድም እስራኤልዊያን የበረሐው ፀሐይ እንዳያደክማቸው የደመናው ምሳሌ ነው ፤ አንድም በመገናኛ ድንኳኑና ሰለሞን ባሰራው ቤተ መቅደስ የሞላው የደመና ምሳሌ ነው።

+++ ጧፍ ፦ ካህኑ ወንጌል ሲያነብ ጧፍ ይይዛል; አልጩለመ ብርሐን አለ ለምንድን ነው ቢሉ ክቡር ዳዊት "ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሐን ነው" ስለሚል ነው። (መዝ 118:105) ወንጌሉ ነውና የሚነበበው ወንጌሉም ለእግራችን መብራት ለመንገዳችንም ብርሃን ስለሆነ ነው። አንድም ክቡር ዳዊት እንዲህ ብሏል፦ "ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ

ብርሃን ነው” (መዝ. 118(119)፥105)። ክቡር ዳዊት ይህን ያለበት የራሱ ታሪክ አለው፦በመካከለኛው ምሥራቅ ከቀኑ ሐሩር የተነሣ በሌሊት መጓዝ የተለመደ ነው። ከጨለማውም ጋር ሽፍቶችና ዘራፊዎች አሳሳቢዎች ስለሆኑ በኅብረት መጓዝ የተለመደ ነው። ጨለማው ጥልቅ መልክአ ምድሩም ገደላማ በመሆኑ የሚረግጡትን በትክክል ለማየት ይቸገራሉ። ሜዳ የረገጡ መስሎአቸው ገደል ሊገቡ ይችላሉ። የሚረግጡትን እርምጃ በትክክል ለማየት እግራቸው ላይ መብራት አስረው ይሄዱ ነበር። ይህ የሚረግጡትን በትክክል ያሳያል።

ነቢዩ በዚህ ምሳሌ፡- “ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው” አለ። ለዚህም ነው ወንጌሉ ሲነበብ ጧፍ የሚያዘው። ሕጉ ለእግራችን መብራት ነውና! አንድም በቤተክርስቲያን ውስጥ በብዛት ሻማ አለ; ይህም እግዚአብሔር በባሕርይው ብርሐን ስለሆነ ነው ፤ ሻማው እየቀለጠ ብርሃን ይሰጣል ይህም ቅዱሳኑ ስለቤተክርስቲያን እንደሻማ እየቀለጡ ለዓለም ብርሐን የመሆናቸው ምሳሌ ነው።

ክፍል 4 ይቀጥላል

መሮከርና መሸለል ወንጌል የሚመስላቸው ፤ እናት ቤተክርስቲያንን ሳያውቋት ወንጌል አልተሰበከም የሚሉ ይፈሩ!

ይህች ድንቅ እናት ቤተክርስቲያን እንኳንስ ተናግራ ሳትናገርም ወንጌልን ትሰብካለች!
እኔስ ድንቅ እናት ቤተክርስቲያን አለችኝ!

Miko ZE Ethiopia
ማዕተብ በአንገታችን ላይ ለምን እናስራለን?
“እኔ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ስንኳ አያድክመኝ።” (ገላትያ 6፡17)
ማዕተብ

የቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም ምልክት ማለት ነው። በኦርቶዶክስ አቢያተ ክርስቲያናት ዘንድ ልዩ ልዩ የክርስትና መለያ ምልክቶችን ማድረግ ከብሉይ ኪዳን በትውፊት/ውርስ/ የተገኘ ነው። በአምልኮተ እግዚአብሔር የተለዩ ውሉደ አብርሃም በግዝረት ይለዩ እንደነበር። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓትና ትውፊት ውስጥ ማዕተብ የተለየ ክብር ያለው የክርስትናችን መለያ/ምልክት/ ነው። ማዕተብ ማሠር በቤተ ክርስትያን ማን ጀመረው?

ማዕተብ በአንገት ማሠር የጀመረው አባት ያዕቆብ ዘአልበረዳኢ የተባለ

በ6ኛውመቶ ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ይኖር የነበረ ቅዱስ አባት ነው።

መስቀል በአንገት ማሠራችን፡-

--> እኛ መስቀልን የምናከብረውና በአንገራችን አሥረን የምንታየው በሌላ ምክንያት ሳይሆን የክርስቶስ ኢየሱስ ኃይል ስለተገለጠበት፣መንፈሳዊ ነፃነት ስለተገኘበት፣ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገርንበት ታላቅ ድልድይ ሆኖ ስለሆነ ነው።

መስቀል በአንገት ማሠራችን ፡-

--> በዚህ ባመንኩት እምነት ክርስቶስ ለኔ በተቀበለው መከራ ታማኝ እሆናለሁ ማለት ነው። ክርስቲያን እንደመሆናችን መጠን

የክርስቶስ የመከራው ተካፋይ መሆናችንን ያመለክታል፡፡

ጠቢቡ ሰሎሞን “ልጄ ሆይ የአባትህን ትዕዛዝ ጠብቅ፡፡ የእናትህንም ሕግ አትተው፡፡ ሁልጊዜ በልብህ አኑረው፡፡ በአንገትህም እሰረው፡፡” ምሳ. 6÷20-22 በማለት የተናገረው ይህንኑ ለማመልከት ነው፡፡”

ቅዱስ ጳውሎስም በገላትያ መልዕክቱ “እኔ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ስንኳ አያድክመኝ፡፡” (ገላትያ 6፡17) ማለቱ ባመንኩት እምነት ክርስቶስ ለኔ በተቀበለው መከራ ታማኝ እሆናለሁ ማለት ነው፡፡

የዘመኑ ተቃዋሚዎች እምነት በልብ ነው ይላሉ፡-
አዎ እምነት በልብ ነው ግን በልብ ይምናምነውን ደግሞ ለሰው መመስከር መጽሀፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ማዕተብ ከአህዛብ የተለየን እና የክርስቶስ ተከታይ መሆናችንን የምንመሰክርበት ነው፡፡ክርስትያን የክርስቶስ ተከታይ መሆናችንን ለአለም የምንመሰክርበት ነው!
ክርስቶስም እንዲህ ብሏል፡-
“በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤” ማቴዎስ 10፡32
ዛሬ ተቃዋሚዎች መስቀሉን መመኪያ መጠጊያ ከማድረጉ ይልቅ

የመስቀሉን ክብር ማቃለል እና መናቅ እና እንደ ዘመናዊነት በመቁጠር የክርስቶስ መስቀል ሕይወቱ በማድረግ ሊገኝ የሚገባውን ፍፁም ሰላም አጥተዋል፡፡
ስለዚህ ምዕመናን በክርስቶስ ደም በተቀደሰው ክቡር መስቀል ተሻሽተን በረከትን ድህነትን ለማግኘት በእምነት በምግባር እስከመጨረሻው ሕቅታ ፀንተን ልንኖር ይገባል፡፡
"ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ!" ገላትያ 6:14
ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

### ጧፍ

፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨፨

ካህኑ ወንጌል ሲያነብ ጧፍ ይይዛል; አልጨለመ ብርሐን አለ ለምንድን ነው ቢሉ ልበ አምላክዳዊት "ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሐን ነው" ስለሚል ነው። (መዝ 119 :105) ወንጌሉ ነውና የሚነበበው ወንጌሉም ለእግራችን መብራት ለመንገዳችንም ብርሃን ስለሆነ ነው።

አንድም ክቡር ዳዊት እንዲህ ብሏል፦ "ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው" (መዝ. 119፥105)። ልበአምላክ ዳዊት

ይህን ያለበት የራሱ ታሪክ አለው፦በመካከለኛው ምሥራቅ ከቀኑ ሐሩር የተነሣ በሌሊት መንዝ የተለመደ ነው፡፡ ከጨለማውም ጋር ሽፍቶችና ዘራፊዎች አሳሳቢዎች ስለሆኑ በኅብረት መንዝ የተለመደ ነው፡፡ ጨለማው ጥልቅ መልክአ ምድሩም ገደላማ በመሆኑ የሚረግጡትን በትክክል ለማየት ይቸገራሉ፡፡ ሜዳ የረገጡ መስሎአቸው ገደል ሊገቡ ይችላሉ፡፡ የሚረግጡትን እርምጃ በትክክል ለማየት እግራቸው ላይ መብራት አስረው ይሄዱ ነበር፡፡ ይህ የሚረግጡትን በትክክል ያሳያል፡፡ ነቢዩ በዚህ ምሳሌ፡- “ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው”

አለ፡፡ ለዚህም ነው ወንጌሉ ሲነበብ ጧፍ የሚያዘው፡፡ ሕጉ ለእግራችን መብራትነውና! አንድም በቤተክርስቲያን ውስጥ በብዛት ሻማ አለ; ይህም እግዚአብሔር በባሕርይው ብርሐን ስለሆነ ነው ፧ ሻማውእየቀለጠ ብርሃን ይሰጣል ይህም ቅዱሳኑ ስለቤተክርስቲያን እንደሻማ እየቀለጡ ለዓለም ብርሐን የመሆናቸው ምሳሌ ነው፡፡

Mekane Selam St. Urael– with ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

ዕጣን

፨፨፨፨፨፨፨

የእጣን ዛፍ የሚገኘው በበረሀ ነው

የቤተ መቅደሥ አገልግሎት ከተጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የፀሎት ማሣረግያ መስዋእት ሆኖ በካህናት ይቀርባል (ኦ.ዘፅአት 30:1) (ኦ.ዘሌዋውያን 16:12-13)

-----

፨፨ ዕጣን የጌታችን ምሣሌ ነው ፨፨

ሰብአ ሠገል ዕጣን አምሀ አድርገው የሰጡትም እንደ እጣን ትሰዋልናለህ ሢሉ ነው (ማቴ 2:11) ። ዕጣን ለሠው ልጆች ሀጥያት እንደሚሠዋ ጌታችንም ሥለ ሠው ልጆች ሁሉ ራሡን ለሞት አሳልፎ ሰጥቷል ።

----

፨፨ ዕጣን የቤተክርሥትያን ምሣሌ ነው ፨፨

<< መአዛዋም እንደ ከርቤና ዕጣን የሆነችው ከልዩ ከነጋዴ ቅመም ሁሉ የሆነችው ይህች ከምድረ በዳ እንደ ጢሥ ምሠሶ የወጣችው ማን ናት? >> ሲል በምድረ በዳ ከተመሰለችው አለም ተለይታ ወደ ሠማይ ንጉሥ ወደ እግዚአብሄር የምትዘረጋ ጸሎቷም የሚሠማላት ቤተክርሥትያንን በእጣን መሥሏታል (መኃልዩ ዘሠለሞን 3:6) ።

-----

፨፨ ዕጣን የምእመን ምሣሌ ነው ፨፨

ቅዱሥ ጳውሎሥ

" በሚድኑትና በሚጠፉት ዘንድ ለእግዚአብሄር የክርሥቶሥ መአዛ

ነንና ለእነዚህ ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ ለእነዚያም ለህይወት የሚሆን የህይወት ሽታ ነን " እንዳለ (2ኛ ቆሮ 2:15-16) ። እጣን በተሠዋ ቁጥር ወደላይ እንደሚወጣ የክርሥትያኖችም ህይወት ከክብር ወደ ክብር ወደ ሠማያዊ ማእረግ ትሄዳለችና ።

-----

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ደግሞ እጣንና ንጹህ ቁርባን (ሥጋ ወደሙ) ከፀሀይ መውጫ እሥከ ፀሀይ መግቢያ ድረሥ ለእግዚአብሄር ሥም እንደሚቀርብ (እንደሚሠዋ) ነቢዩ ሚልክያሥ ተናግሯል (ት.ሚልክያሥ 1:11) ቅድሥት ቤተክርሥትያንም ሥትፈፅመው

ትኖራለች ::
መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም ካህኑን ዘካርያስን ልጅ እንደሚወልድ ሊያበሥረው ወደ መቅደስ በገባ ግዜ ካህኑን ያገኘው እጣን ሲያጥን ነበር (ሉቃስ 1:10) ::
የእጣን መሥዋእት በምድር ላለነው ቀርቶ በሠማይም ቢሆን ለእግዚአብሄር ይቀርባል (ዮ.ራዕይ 5:8 እንዲሁም ዮ.ራዕይ 8:3-4) ::
ስለዚህ የዕጣን መሥዋእት በሀዲስ ኪዳንም አልራተቋረጠምና እናት ቤተክርስትያናችን ተግባራዊ ታደርገዋለች ::::
ወስብሀት ለእግዚአብሄር
ምንጭ: ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

**ይድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ**

***ከበሮ ለምን ይጮሀል?***

***የኔታ ለተማሪዎቻቸው አንድ ጥያቄ አቀረቡ..... "ልጆችከበሮ ለምን ይጮሀል?"***

**የኔታ ....የኔታ .... "በቆዳ ስለተወጠረ ነው"......አለአንድ ተማሪ**

**የዳዊት መሀደሩን በእጁ አንጠልጥሎ ለመመለስ እየቸኮለ። የኔታም "አይደለም አሉ" ሌላኛው ተማሪም...."የኔታ ከእንጨት ስለ ተሰራ ነው" አለ የለበሰውን ለምድ ከፍ ከፍ እያደረገ ........የኔታም ትንሽ ዝም ካሉ በኋላ ..... "አይደለም**

አሉ"...ተማሪው ሁሳ ማውጣት ማውረድ ጀመረ
በሀሳብተወጠረ:: ሁሉም የመጣለትን እና የገመተውን መናገር
ቀጠለግን የሚመልስ ጠፋ::አንድ የሁሉንም ምላሽ በእርጋታ
ይሰማ የነበረተማሪ እጁን አወጣ::...." እሽ ልጄ " አሉ የኔታ
.....ድምፁን ከፍ አደረገና ....,የኔታ እድሉን ስለ ሰጡኝ
አመሰግናለሁ ብሎ እጅ ከነሳ በኋላ ....የኔታ ከበሮየሚጮኸው
"ባዶ ስለሆነ ነው"! አለ::የኔታም የልጁን ምላሽ በማድነቅ
ከወንበራቸው በመነሳት ...ልጄ ተባረክ አሉ::ተማሪዎቹም

በጭብጨባ አጀቡት፡፡የኔታም ቀጠል አደረጉና ..... ልጆች "ባዶ"
የሆነ ነገር ሁሳ ይጮሀል በውስጡ የሆነ ነገር ያለው እቃ ግን
አይጮህም፡፡የተማረም ሰው እንዲሁ ነው፡፡ እውቀት ያለው
አይጮህም፣ ጥበብ ያለው አይጮህም፣ ምንጊዜም ባዶ የሆነ
ሰው ሲጮህ፣ ጥበብ የሌለው ሲፎክር እውቀት የሌለው
ሲያቅራራ ይታያል፡፡ እና ልጆቼ.... እናንተ "ባዶ" እንዳትሆኑ
እውቀትን ጨምሩ፣ በእውቀት ላይ ጥበብን፣ በጥበብ ላይ
እግዚአብሔርን መፍራት ጨምሩ፡፡ምድራችንን በማስተማር
እና

በመስበክ የሞሉ ግን"ባዶ" የሆኑ:: ምድሪቱን በዝማሬ የሞሉ በሐይማኖትእና በምግባር ግን "ባዶ" የሆኑ:: ጌታ ሆይ..... ጌታ ሆይ....የሚሉ ግን ጌታየማያውቃቸው እንደ ሰው ተፈጥረው እንደ እንሰሳ በደመ ነፍስ የሚኖሩ ሰዎች ፣ በዝተዋልና ብለውቁጭ አሉ::ተማሪዎቹም የኔታን አመስግነው ትምህርታቸውን ቀጠሉ::

--------------------------

----------------------

----------------------

ኤዱ እመቤቴ ታሳድግሽ

"መልካም ዕለተ ሰንበት"

ለምን ነጭ ነጠላ እንለብሳለን?

አንዳንዶች ባለማወቅም ይሁን በቅናት ክርስትና ነጠላ ለብሶ ቤተክርስቲያን መሄድ አይደለም ሲሉ ይደመጣሉ። የኦርቶዶክስ

ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ግን መጽሐፍ ቅዱስን ምክንያት አርጋ ምሥጢሩን ከተግባር ጋር ትገልጻለች።
ወደ ቤተ መቅደስ ስንሄድ ነጭ መልበሳችን የተገባ ነው። ነጭ ነጠላ ጋቢ አደግድገን ወይም በትእምርተ መስቀል ለብሰን ቤተመቅደስ ስንቆም የምናስባቸው ምስጢራት አሉ። ለምን በትእምርተ መስቀል እንለብሳለን ካልን የክርስቶስን መከራ ለማሰብ፣ ነጠላው ወደ ግራ ቀኝ በትእምርተ መስቀል አምሳል ይጣፋል። በዚህ ጊዜ ጌታችን በዕለተ አርብ የተቀበላቸው ጸዋትወ መከራ እንዲሁም በቀራንዮ በምልዕልተ

መስቀል መሰቀሉን ያስታውሰናል። ይኸውም የተመሳቀለ ነጠላ የሚመለከትም ሁሉ የጌታችንን መከራ መስቀል መቀበሉን ያስባል። የምናጣፋው ነጠላ ነጭ የሆነባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ እነዚህ ከታች የተጠቀሱት ምክንያቶች ሰፊ ትምህርት ቢኖራቸውም እኔ ግን ባጭሩ እንዲህ አቀረብኩላችሁ፦

፩. የሚጠብቀንን ሰማያዊ ክብር በማሰብ ነጭ እንለብሳለን"..... ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ እስከመቼ አትፈርድም? ደማችንንስ በምድር ላይ በሚኖሩት ላይ እስከመቼ ድረስ አትበቀልም አሉ ለእያንዳንዳቸው ነጭ ልብስ ተሰጣቸው....." /ራዕ.፮፥፱-፲፩/"

ከዚህም በኋላ አየሁ እንሆም አንድ እንኳን ሊቆጥራቸው የማይችል ከህዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባም የዝንጣፊም በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊትቆሙ"
/ራዕ.፯፥፱/

፩. ቅዱሳን መላእክት ከእኛ ጋር መሆናቸውን ማሰብ".....

ማርያም ግን እያለቀሰች ከመቃብር በስተ ውጪ ቆማ ነበር፡፡ስታለቅስም ወደ መቃብር ዝቅ ብላ ተመለከተች ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው የጌታ የኢየሱስ ሥጋ በነበረበት ቦታ አንዱ በራስጌ ሌላው በግርጌ ተቀምጠው አየች፡፡"

/ዮሐ.፳፥፲፩-፲፪/ ታድያ እንደ መላእክት ለብሶ በቤተክርስቲያን ማገልገል ምኑ ነው የሚያስወቅሰው ያሚያሳፍረው ያኮራል እንጂ!።
፫. ከጌታችን ጋር እንዳለን እናስባለን".....
ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራረ ለብቻቸው አወጣቸው። በፊታቸውም መልኩ ተለወጠ ፊቱም እንደ ፀሐይ አበራ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ሆነ።" /ማቴ.፲፯፥፩-፪/ ስለዚህም ነጠላ መልበስ መንፈሳዊ ትርጉም አለውና ወንዶች ብንሆን በኪዳኑ፣ በቅዳሴውና በንግሱ ላይ ያለ ነጠላ ከምንሄድ

ነጠላ ብንለብስ እህቶቼም ሥርዓቱን የጠበቀ ነጠላ ለብሰን ከላይ የተጠቀሱትን እያሰብን በቤቱ ብንገኝ መልካም ነው፡፡

<< አባቶች የሠሩትን የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ >> /ምሳሌ.፳፪÷፳፰/

ሁላችንም ሥርዓተ ቤተክርስትያንን እንድንጠብቅ ልቦና ይስጠን፡፡ እግዚአብሔር ሁላችንንም እንደ ፍላጎታችን ሳይሆን እንደ እርሱ ፈቃድ እንድንመራ ዓይነ ልቦናችንን ያብራልን! ይህ እራስን መግዛት ለቃሉ አለመታዘዝ ብዙዎቻችን ጋር ያለ ችግር ነው ይህ የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጣችን ሳይኖር የዓለምን ፍቅር አብልጠን

ምን ችግር አለው? እያልን በእግር ብቻ በቤቱ መመላለስ ስለለመድን ነው:: ትልቁ ችግር ያመጣው ምን ችግር አለው? ነው:: ለዚህም ማሳያ እንደ ፕሮቴስታንት ተሃድሶ መናፍቃን እምነት ያለ ዶግማና ቀኖና በራሳችን አስተያየት የምንጓዝ ቢሆን ብዙ ድርጅት በሆንን ነበር፤ ግን አንድ ሀሳብ አንድ አላማ የሚያረገንን ዶግማና ቀኖና ቤተክርስቲያናችን ሰርታልናለች፤ ስለዚህም ትክክል ያልሆነውን የዓለም ስርአት ስለተለማመድን ነው እንደ ቤተክርስቲያን ስርዓት ለመመላለስ ይቸግረናል ከመምህረ ንሰሃችን (ንስሃ አባታችን) ጋር በመመካከር፤ በግልና በማህበራዊ

ጸሎቶች በመትጋት፤ አንዱ ለሌላው በመጸለይ፤ ሁል ግዜ ቅዱሳት መጽሐፍትን በማንበብና ሊያዘናጉን ከሚችሉ ሁኔታዎች በመራቅ ለእግዚአብሔር ሕግ መገዛት እንችላለን ትእዛዙን ፈጽመን ለመኖር የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ሁላችንንም ይርዳን!!! ምንጭ፦ የየካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን መልአከ ሠላም ሰንበት ትምህርት ቤት

ጸ ናጽል
ስንዴ ና # ወይን ለምን ለጌታችን ስጋና ደም ተመረጠ???
ድርሳንና ገድላት ጥያቄ

በቅዳሴ ላይ ወንጌል ሲነበብ ጥላ ይዘረጋል

ማዕተብ በአንገታችን ላይ ለምን እናስራለን?

*ጧፍ*

*ዕጣን*

*ከበሮ ለምን ይጮሀል?*

ለምን ነጭ ነጠላ እንለብሳለን?

Samson Desu

//,,,ለምን ነጭ ነጠላ እንለብሳለን..?,,,,,//

ሼር በማድረጎት የሚገኘው ጥቅም....!

1.. ይህን ያላወቁ ሌሎች በእርሶ ምክንያት ያውቃሉ.!

2...ወንጌልን ለሌሎች ያደርሳሉ...!

1. ጌታን አብነት በማድረግ

ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል የምሥጢር ሐዋርያት የሚባሉትን ጴጥሮስን ፣ ዮሐንስንና ያዕቆብን ይዞ ወደ ደብረ ታቦር ወጥቶ ደቀ መዛሙርቱ እያዩት ልብሱ ነጭ ሆኖ ነበር፤"በፊታቸውም ተለወጠ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ።"(ማቴ17:2) እኛም ሊያድነንና አርአያ ሆኖ ሊያስተምረን ሰው የሆነውን ጌታችንን አብነት በማድረግ ነጭ ነጠላን ለብሰን የደብረ ታቦር ምሳሌ ወደሆነችው ቤተክርስቲያን እንሰባሰባለን።

2. ቅዱሳንን አብነት በማድረግ

በዮሐንስ ራእይ ምእራፍ 6 ላይ በዐጸደ ነፍስ ስላሉ ቅዱሳን የሚከተለው ተጽፎ ይገኛል:: "አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ:: በታላቅ ድምፅም እየጮኹ:: ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ:: ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፥ እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪፈጸም

ድረስ፥ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው።"(ራዕ.6፡9-11) በራእይ ሰባትም ባለራእዩ እንዲህ ብሏል። "ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤" (ራዕ.7:9)እኛም ቅዱሳኑን አብነት በማድረግና ከበጉ ቀኝ ነጭ ለብሰን የመቆም ተስፋን በመሰነቅ ነጭ ነጠላን እንለብሳለን።

3. መላእክትን አብነት በማድረግ

ጌታ በፈቃዱ ነፍሱን ከሥጋው በለየ በሦስተኛው ቀን መግደላዊት

ማርያም ወደ መቃብሩ በሔደች ጊዜ የጌታ ትንሣኤን የሚያበሥሩ ሁለት ነጭ የለበሱ መላእክትን አግኝታ ነበር፦"ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው የኢየሱስ ሥጋ ተኝቶበት በነበረው አንዱ በራስጌ ሌላውም በእግርጌ ተቀምጠው አየች።" (የዮሐንስ ወንጌል 20:12) እኛም ቅዱሳን መላእክትን አብነት በማድረግ ነጭ ለብሰን የትንሣኤያችን ማእከል በሆነች ቤተ ክርስቲያን እንሰባሰባለን።

4. ክርስትና በሰማያዊ ተስፋ የተሞላ ብርሃናማ ሕይወት ነውና ይህን ተስፋችንን በማሰብ ነጭ ነጠላን እንለብሳለን። ስለዚህ መስቀልያ አጣፍተን መስቀሉን

በማሰብ የምንለብሰው ነጠላ እንዲሁ በዘፈቀደ የሚለበስ አለመሆኑን በመገንዘብ ሥርዐቱን ልንተገብር ይገባል፡፡

ወስብሃት ለእግዚአብሔር
ወለ ወላዲተ ድንግል
ወለ መስቀሉ ክቡር አሜን፡፡

ቅድስት አርሴማ ደጓ እናቴ

የሰጎን እንቁላል ለምን የኛ የቤተ ክርስቲያን መስቀል ላይ ይሰቀላል
What is the significance of the tradition of using ostrich egg shells on Tewahido church crosses?
አሁን ተሰለጠነና እየቀረ ሄደ እንጂ

፤ በቤተ ክርስቲያኖቻችን ጉልላቶች የሚቀመጡት መስቀሎች እታች እንደሚታየው በጠንካራውና በቀላሉ በማይሰበረው በሰጎን እንቁላል ያሸበረቁ ነበሩ። አሁንም አልፎ አልፎ ይታያሉ።
የሰጎኑ እንቁላል ትልቅ ፤ ነጭና ፣ ጸሀይ ወይም ጨረቃ ሲመታው የሙያንጸባርቅ በመሆኑ ፤ ምእመናንን የሚስብና የሚጋብዝ ይሆናል። ሁለተኛውና ብዙ ምስጢር ያለው ግን ከሰጎን ጋር የተገናኘ ነው። ሰጎን እንቁላሏን በቅርብና በፍቅር ተንከባካቢ ናት። ከእንቁላሏ ብዙ አትርቅም ፤ እንቁላሏን የቀረበ ፤ አንበሳም ቢሆን ወዮለት። ቤተክርስቲያንንም

ምእመናን ጠንቅቀው እንዲንከባከቡና እንዲጠብቁ የሰጎን እንቁላል ለማስታወኻሻነት ይጠቅማል።

The Ethiopian Tewahido church has used ostrich egg shells on church top crosses for centuries. There are two reasons for this unique custom. The first is that these large, white and shiny objects which reflect the light of the sun and the moon serve as glowing orbs that parishioners and pilgrims can see from far away.

The second reason is to use

it as a metaphor from the loving care ostriches give their eggs. Ostriches fuss over their eggs, lovingly turning them and incubating them lovingly. They are never too far and are fearless in protecting their eggs even from lions let alone small animals. The church cross ostrich eggs instruct followers to care, support and protect their faith like the ostrich.

3 hours ago · Public · in Timeline Photos

View Full Size · Send as Message ·

Report
137 people like this.
Write a comment...
Comment
Attach a Photo · Mention Friends
Tadi Sisayi
**የሰጎን እንቁላል ወድቆ አይሰበርም እኔ በእግዚአብሔር በፍጹም አላፍርም**
**ተዋህዶ እምነኤ ትኑር ለዘላለም**
Like · 3 · Reply · Report · 1 hour ago
Menbere Mariam Girma
EGZIABHER YEMESEGEN amen
Like · 1 · Reply · Report · 2

hours ago
Sarah Kasa
የሰጎን እንቁላል የሚፈለፈለው በአይን እይታነው:: እናም እስኪፈለፈል ድርስ እናትየዋ ታየዋለት ያለማቋረጥ ማለት ነው እኔና እንንተንም አምላካችን አለም ከተፈጠርች ጀምሮ ለሰከንድ ሳያንቀላፍእስከመጨረሻ ይጠብቀናል ስሙ ይክበር ይመስገን:: እናም እናም ጉልላቱ ላይ የሰጎን እንቊላል የሚቀመጠው ለዚህ ነው የቤተክርስቲያን መሰረቱ ክርስቶስ መሆኑን ለማሳውቅ ነው ::

Alem Taye

የቤተ ክርስቲያን ደጃፉን ለምን እንደሚሳለሙ ያውቃሉ?

በትእምርተ መስቀል ከአማትበን በኋላ የቤተ መቅደሱን ደጃፍ በእምነት ስንሳለም ተመልክተው የሚገርማቸው አይጠፉም እንዲህ ያሉ ሰዎች ዐጸዱን ደጃፉን በበሩን መስኮቱን መሳለማችን እነርሱ እንደሚያስቡት ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ደጃፉን የምንሳለምበት የተለያየ ምክንያት አለን፡፡

፩. ቤተ መቅደሱን እንዲሁ በውስጡና በዙሪያው ያለውን የነካ ስለሚቀደስበት

“የቅብዐት ዘይትን ወስደህ ማደሪያውን በእርሱም ያለውን ሁሉ ትቀድሳለህ ቅዱስም ይሆናል” ሲል

ለሙሴ አዞታል ኦሪ ዘፀ ፵÷፱/40÷9/ እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱና በዙሪያው ያሉ ሁሉ እንዲቀደሱ አዟል፡፡ደብተራ ኦሪት ሲተከል የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሲሰራ ዙሪያው በቅብዓ ቅዱስ ተቀድሷል የቤተ መቅደሱ ደጃፍ መሳለም መሳም የሚያስፈልገው ለዚህ ነው፡፡ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ደጃፉ በቅብዓ ሜሮን የከበረ የተቀደሰ ስለሆነ የሚሳለመው የሚስመው የሚተባበሰው ሁሉ ይቀደሳል፡፡

፪. ቤተ መቅደስ የክርስቶስ ማደሪያ ስለሆነ

በሌላ በኩል ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ዘርፉ ልብሱ

መቅደሱ ናት፡፡ ኤፌ ፭፥፳፫/5፥23/፡፡ አካል ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር ያለውን ሁሉ እንደሚይዝ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት ሲባል የቤተ ክርስቲያኑ አካል ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ስለዚህ አካሉ የሆነችው ይህች ቤተ ክርስቲያን/ቤተ መቅደስ/ መሳለም መተባበስ የጌታችንን የልብሱን ዘርፍ በመንካቷ አስራ ሁለት በዓመት ሙሉ ደም ሲፈሳት ኖራ እንደተፈወሰችው ሴት የእምነት ጥንካሬ ምልክት ነው ሉቃ ፰፥፵፫-፵፰ /8፥43-48/፡፡በእምነት ለሚሳለም በእምነት ለሚኖር ሰው የቤተክርስቲያን ደጃፎቿ ዐጸዱ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ያለው

ጠበል አጥሩ ቅጥሩ ውስጡ ውጪው ሁሉ ፈውስና መድኃኒት ይሆነዋል፡፡

፫. ቤተ መቅደሱ የመለኮት ማደሪያ ስለሆነ

ቤተ ክርስቲያን/ቤተ መቅደሱ/ የመለኮት ማደሪያ ነው፡፡በሰማይ በክብር የሚኖር እግዚአብሔር በቤተ መቅደሱን በረድኤት ያድራል፡፡ ቤተ መቅደሱን የክብሩ መገለጫ አድርጎታልና፡፡ "አሁንም ስሜ ለዘለዓለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለው ቀድሻለውም ዐይኖቼና ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናሉ" ፪/2/ ዜና፯፥፲፮ /7፥16/ "ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን" መዝ ፻፴፩፥፯/131፥7/ እንዲል ቤተ

መቅደሱ የእግዚአብሔር ማደሪያ ስለሆነ ደጃፉ አጥሩ ቅጥሩ ሁሉ የተቀደሰ በበረከት የተሞላ ነው፡፡ ስለዚህ ወደ ቤተ መቅደስ የሚቀርብ ሰው ይህን እያሰበ ይሳለማል፡፡

ስለዚህ ሰው ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ደጃፏን /ደጀ ሠላሟን/ "ሠላም ለኪ ቤተ ክርስቲያን አምሳለ ኢየሩሳሌም ቅድስት" /ቅድስት የምትሆን የሰማያዊ ኢየሩሳሌም አምሳል የሆንሽ ቤተ ክርስቲያን ሆይ ሠላምታ ይገባሻል/ እያልን ደጃፏን አጥሯን የምንሳለመው ወስብሐት ለእግዚአብሔር ለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር፡፡

1. የከበሮ ክፍል ምሳሌያዊ ትርጉም
2. የከበሮ አመታት

3. መብራት ለምን እናበራለን?
4. ክርስቲያናዊ አለባበስ
5. መቁዋሚያ
6. ከበሮ ለምን ይጮሀል ???
7. የከበሮ ክፍል ምሳሌያዊ ትርጉም
8. ጧፍ
9. ዕጣን
10. ከበሮ ለምን ይጮሀል?
11. ማዕተብ
12. የቤተክርስትያን ከበሮ እና ድንቅ ምሳሌው
13. ክርስቲያናዊ አለባበስ....ለመላው ክርስቲያኖች መሰልጠን ወይስ መሰይጠን?

14. መቁዋሚያ
15. ለምን ነጭ ነጠላ እንለብሳለን?
16. ጽንሃ ~
17. ጸናጽል
18. በሚሞት ስጋችሁ ሐጢያት አይንገስ
19. ጸ ናጽል
20. ስንዴ ና # ወይን ለምን ለጌታችን ስጋና ደም ተመረጠ???
21. ድርሳንና ገድላት ጥያቄ
22. በቅዳሴ ላይ ወንጌል ሲነበብ ጥላ ይዘረጋል
23. ማዕተብ በአንገታችን ላይ ለምን እናስራለን?
24. ጧፍ

25. ዕጣን
26. ከበሮ ለምን ይጮሀል?
27. ለምን ነጭ ነጠላ እንለብሳለን?
28. ,,ለምን ነጭ ነጠላ እንለብሳለን..?
29. የሰጎን እንቁላል ለምን የኛ የቤተ ክርስቲያን መስቀል ላይ ይሰቀላል
30. የቤተ ክርስቲያን ደጃፉን ለምን እንደሚሳለሙ ያውቃሉ?

ከመስቀሉ ስር ነው አድራሻዬ and 14 others .
የቤተ ክርስቲያን ደጃፉን ለምን

እንደሚሳለሙ ያውቃሉ?
በትእምርተ መስቀል ከአማትበን በኋላ የቤተ መቅደሱን ደጃፍ በእምነት ስንሳለም ተመልክተው የሚገርማቸው አይጠፉም
እንዲህ ያሉ ሰዎች ዐጸዱን ደጃፉን በበሩን መስኮቱን
መሳለማችን እነርሱ እንደሚያስቡት ያለ ምክንያት አይደለም፡፡
ደጃፉን የምንሳለምበት የተለያየ ምክንያት አለን፡፡
፩. ቤተ መቅደሱን እንዲሁ በውስጡና በዙሪያው ያለውን የነካ ስለሚቀደስበት
“የቅብዐት ዘይትን ወስደህ ማደሪያውን በእርሱም ያለውን ሁሉ ትቀድሳለህ ቅዱስም ይሆናል” ሲል

ለሙሴ አዞታል ኦሪ ዘፀ
፵፥፱/40፥9/
እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱና በዙሪያው ያሉ ሁሉ እንዲቀደሱ አዟል፡፡ደብተራ ኦሪት ሲተከል የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሲሰራ ዙሪያው በቅብዓ ቅዱስ ተቀድሷል የቤተ መቅደሱ ደጃፍ
መሳለም መሳም የሚያስፈልገው ለዚህ ነው፡፡ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ደጃፉ በቅብዓ ሜሮን የከበረ የተቀደሰ ስለሆነ የሚሳለመው የሚስመው የሚተባበሰው ሁሉ ይቀደሳል፡፡
፪. ቤተ መቅደስ የክርስቶስ ማደሪያ ስለሆነ
በሌላ በኩል ቅዱስ ጳውሎስ

እንደተናገረ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ዘርፉ ልብሱ መቅደሱ ናት፡፡ ኤፌ ፭÷፳፫/5÷23/፡፡ አካል ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር ያለውን ሁሉ እንደሚይዝ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት ሲባል የቤተ ክርስቲያኑ አካል ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ስለዚህ አካሉ የሆነችው ይህች ቤተ ክርስቲያን/ቤተ መቅደስ/ መሳለም መተባበስ የጌታችንን የልብሱን ዘርፍ በመንካቷ አስራ ሁለት በዓመት ሙሉ ደም ሲፈሳት ኖራ እንደተፈወሰችው ሴት የእምነት ጥንካሬ ምልክት ነው ሉቃ

፳፥፵፫-፵፰ /8፥43-48/፡፡በእምነት ለሚሳለም በእምነት ለሚኖር ሰው የቤተክርስቲያን ደጃፎቿ ዐጸዱ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ያለው ጠበል አጥሩ ቅጥሩ ውስጡ ውጪው ሁሉ ፈውስና መድኃኒት ይሆነዋል፡፡

፫. ቤተ መቅደሱ የመለኮት ማደሪያ ስለሆነ

ቤተ ክርስቲያን/ቤተ መቅደሱ/ የመለኮት ማደሪያ ነው፡፡ በሰማይ በክብር የሚኖር እግዚአብሔር በቤተ መቅደሱን በረድኤት ያድራል፡፡ ቤተ መቅደሱን የክብሩ መገለጫ አድርጎታልና፡፡ “አሁንም ስሜ ለዘለዓለም በዚያ

ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለው ቀድሻለውም ዐይኖቼና
ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናሉ”
፪/2/ ዜና፯÷፲፮ /7÷16/
“ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን” መዝ ፻፴፩÷፯/131÷7/ እንዲል
ቤተ መቅደሱ የእግዚአብሔር ማደሪያ ስለሆነ ደጃፉ አጥሩ
ቅጥሩ ሁሉ የተቀደሰ በበረከት የተሞላ ነው። ስለዚህ ወደ
ቤተ መቅደስ የሚቀርብ ሰው ይህን እያሰበ ይሳለማል።
ስለዚህ ሰው ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ደጃፏን /ደጀ ሠላሟን/
“ሠላም ለኪ ቤተ ክርስቲያን አምሳለ ኢየሩሳሌም ቅድስት” /
ቅድስት የምትሆን የሰማያዊ

ኢየሩሳሌም አምሳል የሆንሽ
ቤተ ክርስቲያን ሆይ
ሠላምታ ይገባሻል/ እያልን ደጃፏን
አጥሯን የምንሳለመው
ወስብሐት ለእግዚአብሔር ለወላዲቱ
ድንግል ወለመስቀሉ
ክቡር::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተ ክርስቲያ .
"+"ማዕተብ በአንገታችን ላይ ለምን
እናስራለን?

“እኔ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ስንኳ አያድክመኝ።” (ገላትያ 6፡17)

ማዕተብ

የቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም ምልክት ማለት ነው።

በኦርቶዶክስ አቢያተ ክርስቲያናት ዘንድ ልዩ ልዩ የክርስትና መለያ ምልክቶችን ማድረግ ከብሉይ ኪዳን በትውፊት/ውርስ/ የተገኘ ነው።

በአምልኮተ እግዚአብሔር የተለዩ ውሉደ አብርሃም በግዝረት ይለዩ እንደነበር።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
እምነት ሥርዓትና ትውፊት ውስጥ ማዕተብ
የተለየ ክብር ያለው የክርስትናችን መለያ/
ምልክት/ ነው::
ማዕተብ ማሠር በቤተ ክርስትያን ማን
ጀመረው?
ማዕተብ በአንገት ማሠር የጀመረው አባት
ያዕቆብ ዘአልበረዳኢ የተባለ በ6ኛውመቶ ክፍለ
ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ይኖር የነበረ
ቅዱስ አባት ነው::

መስቀል በአንገት ማሠራችን፡-

--> እኛ መስቀልን የምናከብረውና በአንገራችን አሥረን የምንታየው በሌላ ምክንያት ሳይሆን የክርስቶስ ኢየሱስ ኃይል ስለተገለጠበት፣መንፈሳዊ ነፃነት ስለተገኘበት፣ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገርንበት ታላቅ ድልድይ ሆኖ ስለሆነ ነው፡፡

መስቀል በአንገት ማሠራችን ፡-

--> በዚህ ባመንኩት እምነት ክርስቶስ ለኔ በተቀበለው መከራ ታማኝ እሆናለሁ ማለት ነው፡፡ ክርስቲያን እንደመሆናችን

መጠን
የክርስቶስ የመከራው ተካፋይ
መሆናችንን
ያመለክታል፡፡
ጠቢቡ ሰሎሞን “ልጄ ሆይ
የአባትህን ትዕዛዝ
ጠብቅ፡፡ የእናትህንም ሕግ
አትተው፡፡ ሁልጊዜ
በልብህ አኑረው፡፡ በአንገትህም
እሰረው፡፡”
ምሳ. 6÷20-22 በማለት የተናገረው
ይህንኑ
ለማመልከት ነው፡፡”
ቅዱስ ጳውሎስም በገላትያ
መልዕክቱ “እኔ
የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ
ተሸክሜአለሁና

ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ስንኳ
አያድክመኝ::” (ገላትያ 6፡17)
ማለቱ
ባመንኩት እምነት ክርስቶስ ለኔ
በተቀበለው
መከራ ታማኝ እሆናለሁ ማለት
ነው::
የዘመኑ ተቃዋሚዎች እምነት
በልብ ነው
ይላሉ፡-
አዎ እምነት በልብ ነው ግን በልብ
ይምናምነውን ደግሞ ለሰው
መመስከር
መጽሀፍ ቅዱሳዊ ነው::ማዕተብ
ከአህዛብ
የተለየን እና የክርስቶስ ተከታይ
መሆናችንን

የምንመሰክርበት ነው፡፡ክርስትያን የክርስቶስ
ተከታይ መሆናችንን ለአለም የምንመሰክርበት
ነው!
ክርስቶስም እንዲህ ብሏል፡-
“በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ
በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት
እመሰክርለታለሁ፤” ማቴዎስ 10፡32
ዛሬ ተቃዋሚዎች መስቀሉን መመኪያ
መጠጊያ ከማድረጉ ይልቅ የመስቀሉን ክብር
ማቃለል እና መናቅ እና እንደ ዘመናዊነት

በመቁጠር የክርስቶስ መስቀል
ሕይወቱ
በማድረግ ሊገኝ የሚገባውን ፍፁም
ሰላም
አጥተዋል፡፡
ስለዚህ ምዕመናን በክርስቶስ ደም
በተቀደሰው
ክቡር መስቀል ተሻሽተን በረከትን
ድህነትን
ለማግኘት በእምነት በምግባር
እስከመጨረሻው ሕቅታ ፀንተን
ልንኖር
ይገባል፡፡
"ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ
መስቀል በቀር
ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ!"
ገላትያ 6:14

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር
# (ያዎቁትን ማሳዎቅ በጎነት ነው)